# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

እሁድ | 83 ዓመት ቁጥር 188 መጋቢት 8 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# “ከስምምነቱ በኋላ በትግራይ ሰፊ ድጋፍ አድርገናል፤ በቀጣይም በውይይት ታግዘን ብዙ እንሠራለን”

- ጠቅላይ ሚኒስትር
  ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)



**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- ከፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት በኋላ በትግራይ ክልል በርካታ ድጋፍ አድርገናል፤ በቀጣይም በውይይትና በመግባባት መንፈስ ታግዘን ብዙ እንሠራለን ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተናገሩ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከትግራይ ክልል የማህበረሰብ ተወካዮች ጋር ሰሞኑን ውይይት ባደረጉበት ውይይት እንዳስታወቁት፤ ከስምምነቱ በኋላ በክልሉ መረጋጋት ተፈጥሯል፣ መንግሥትም የተለያዩ ድጋፎችን እያደረገ ነው።

በክልሉ የመረጋጋት ስሜት መፈጠሩንና ክልላዊ መንግሥት የመመስረት እንዲሁም ሕጋዊ የሆነ የለውጥ ሂደቶች መደረጋቸውን አስታውሰው፤ ክንውኖቹ ሙሉ እንዲሆኑ ደግሞ ከማህበረሰቡ ጋር ውይይት ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ የፌዴራል መንግሥት ለዚሁ ተግባር ትብብር በማድረግ ከማህበረሰቡ ጋር ምክክር ማድረጉን አስረድተዋል።

አሁንም ድረስ ጦርነት የሚፈልጉ ሰዎችን የትግራይ ሕዝብ በቃችሁ ሊላቸው ይገባል ያሉት ዶክተር ዐቢይ፤ ትግራይ ክልል በልማትና በተለያዩ ሥራዎች የሚቀየርበት ማንኛውም መንገድ ካለ በሙሉ ልብ

“ከስምምነቱ በኋላ በትግራይ ሰፊ...ወደ ገጽ 5 ዞሯል











# ሕዝባዊ ውይይቶቹ ለሀገር ግንባታ መሠረት የሚጥሉ ናቸው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ሕዝባዊ ውይይቶቹ ሀገረ መንግሥቱንም ሆነ የሀገር ግንባታ ሂደቱን ዘላቂ መሠረት እንዲኖረው የሚያግዙ ናቸው ሲሉ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትሩ ለገሰ ቱሉ (ዶ/ር) ገለጹ።

ባሳለፍናቸው ሳምንታት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በሀገሪቱ ከሚገኙ ክልሎች ከተውጣጡ የማህበረሰብ ክፍሎችና የተለያዩ የመንግሥት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ከሕዝብ ጋር ያደረጓቸው የተለያዩ ውይይቶችን አስመልክተው መልዕክት አስተላልፈዋል። በመልዕክታቸው ሕዝባዊ ውይይቶቹ ማህበረሰቡ

...ወደ ገጽ 5 ዞሯል

# ኮሚሽኑ የሁሉንም ማህበረሰብ ሃሳብ በምክክር መድረኩ ለማቅረብ እየሠራ ነው

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የሁሉንም ማህበረሰብ ክፍል ሃሳብ ወደዋናው የምክክር መድረክ ለማቅረብ እየሠራ መሆኑን አስታወቀ።

ኮሚሽኑ ትናንት አጀንዳ ለማሰባሰብ ባዘጋጀው የአሠራር ሂደት ላይ ውይይት ባካሄደበት ወቅት የኮሚሽኑ ዋና ሰብሳቢ ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ እንደተናገሩት፤ በሀገራዊ ምክክር መድረኩ ሳይወከል የሚቀር ምንም ዓይነት የማህበረሰብ ክፍል አይኖርም። ኮሚሽኑም በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ሁሉ የኅብረተሰብ ተሳትፎ እንዲኖር ዋና ትኩረቱ አድርጎ እንደሚሠራ ገልጸዋል።

ኮሚሽኑ የሁሉንም...ወደ ገጽ 5 ዞሯል



ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ



## “የመንገድ ግንባታው በመጓተቱ ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውስ ተዳርገናል”

-የከምባታ ዞን ነዋሪዎች

## “መንገዱን በቀጣይ ዓመት ለተሽከርካሪ ክፍት ለማድረግ ታቅዷል”

-የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር

ገጽ 4










ወይዘሮ አይናለም ንጉሴ

## ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ሥርዓቱ የታክስና ቀረጥ ገቢን ለማሳደግ ይረዳል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ሥርዓት ዜጎች ለግብር ያላቸው አመለካከት በመሻሻሉ የታክስና ቀረጥ ገቢ ከጊዜ ወደ ጊዜ ለማሳደግ እንደሚረዳ የገቢዎች ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የገቢዎች ሚኒስቴርና የጉምሩክ ኮሚሽን "ግብር ለሀገር ክብር" በሚል መሪ ሃሳብ ከዘርፉ ምሁራንና ከንግድ ማህበራት ጋር በታክስና ቀረጥ ሕግ ተገዥነት ዙሪያ ትናንት ውይይት አካሂደዋል፡፡

በወቅቱ የገቢዎች ሚኒስትር ወይዘሮ አይናለም ንጉሴ እንደገለጹት፤ ከሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ መለኪያዎች አንጻር ሲታይ ብዙ ሥራ ቢጠበቅም ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ሥርዓት በመዘርጋቱና ዜጎች ለግብር ያላቸው አመለካከት እየተስተካከለ በመምጣቱ የታክስና ቀረጥ ገቢ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ነው፡፡

የኢትዮጵያ አጠቃላይ የታክስ ገቢ ከሀገራዊ ምርት አንጻር ሲታይ ዝቅተኛ አፈጻጸም አለው ያሉት ሚኒስትሯ፤ ገቢውን ይበልጥ ማሳደግ እንደሚገባም ጠቁመዋል።

የታክስና የቀረጥ ሕግ ተገዥነት ዙሪያ ተከታታይ ውይይቶች በማድረግ የታክስ ቁጥጥር ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች እየተቀረፉ መሆኑን አንስተው፤ የታክስ ግብር አሰባሰብን ለማዘመንና የገቢ አሰባሰቡን ወደሚጠበቅበት ደረጃ ለማድረስ ከዘርፉ ምሁራንና ከንግዱ ማህበረሰብ ጋር ይበልጥ እንደሚሠራ አመላክተዋል፡፡

በተለይ ምሁራን በግብር ምርመራ፣ በግብር አያያዝ፣ በኦዲት መከላከል፣ በወጪና ገቢ ንግድ፣ በሀሰተኛ ደረሰኝ ቁጥጥርና በተያያዥ ጉዳዮች ላይ ያላቸው ልምድ ለሚኒስቴሩና ለኮሚሽኑ ሠራተኞች አስፈላጊ መሆኑን አስረድተዋል።

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ፤ የሚጠበቅባቸውን ታክስና ቀረጥ በተገቢውና በወቅቱ የሚከፍሉ የንግዱ ማህበረሰብ ክፍሎች አንዳሉ በተቃራኒው ታክስና ቀረጥ የሚያጭበረብሩ፣ በኮንትሮባንድ ንግድ ላይ የተሠማሩ፣ በግብይት ወቅት ሀሰተኛ ደረሰኝ የሚጠቀሙና ደረሰኝ የማይቆርጡ ድርጅቶችና ግለሰቦች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም፡፡

በሕገወጥ ንግድ የተሰማሩትን ተቋማትና ግለሰቦች በተቻለ አቅም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ወደ ሕጋዊ ሥርዓት እንዲገቡ የማድረግ ሥራ መጠናከር አለበት ሲሉ ተናግረዋል። ነገር ግን በሕገ ወጥነታቸው ጸንተው የሚቀጥሉ ከሆነ ፍትሐዊ የንግድ ውድድሩን ስለሚያቀጭጨው በሕግ አግባብ ርምጃ ይወሰዳል ብለዋል።

በአንጻሩ ግብር ከፋዮችን የሚመጥን አገልግሎት መስጠት ወሳኝና ተገቢ መሆኑን የገለጹት ሚኒስትሯ፤ እንደ ተቋም የገቢውን ዘርፍ ለማሳደግ ምቹና ቀልጣፋ አገልግሎቶችን ለመስጠት የዲጂታላይዜሽን ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ጠቁመዋል።

በርካታ ግብር ከፋዮች ግብራቸውንና ቀረጣቸውን በኤሌክትሮኒክስ ሥርዓት እንዲከፍሉ አሠራሮች ተመቻችተዋል ያሉት ወይዘሮ አይናለም፤ በቀጣይ ሁሉንም ግብር ከፋይ በኤሌክትሮኒክስ ክፍያ እንዲስተናገዱ ለማድረግ በሙሉ አቅማችን እየሠራን ነው ሲሉ ተናግረዋል።

አልፎ አልፎ የሚስተዋሉ የሥነ ምግባር ችግሮችን ለመቅረፍ ከሰዎች ንክኪ ነጻ የሚያደርጉ አሠራሮች እየተዘረጉ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

## 3 ነጥብ 7 ሚሊዮን ዜጎችን የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ የሚያደርግ ፕሮጀክት ይፋ ሆነ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ከዓለም ባንክና ከውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ከ3 ነጥበ 7 ሚሊዮን በላይ ዜጎችን የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተጠቃሚ የሚያደርግ ፕሮጀክት በይፋ አስጀምሯል፡፡

በወቅቱ የባንኩ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ጌታቸው ዋቄ፤ ያልተማከለ የኤሌክትሪክና መብራት አቅርቦት ፕሮጀክት በአጠቃላይ 500 ሚሊዮን ዶላር በጀት እንደተያዘለት አስታውሰው፤ የዚሁ ግዙፍ የፕሮጀክት አካል የሆነውና በ42 ሚሊዮን ብር የሚተገበረው ንዑስ ፕሮጀክትም ከ3 ነጥበ 7 ሚሊዮን በላይ ዜጎችን ተጠቃሚ ያደርጋል ብለዋል። ያልተማከለ የኤሌክትሪክና መብራት አቅርቦት ፕሮጀክት በዋናነት ታልሞ የሚተገበረው ለማህበረሰቡ የቤት ውስጥ አገልግሎት፣ ለማህበራዊና የንግድ ተቋማትን አስተማማኝ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ለማሻሻል መሆኑን ጠቁመዋል።

ምክትል ፕሬዚዳንቱ እንዳመለከቱት፤ ፕሮጀክቱ በከተማ፣ በገጠር እንዲሁም የኤሌክትሪክ መስመር ባልተዳረሰባቸው የገጠር አካባቢዎች ለቤት ውስጥ፣ ለንግድና ማህበራዊ ተቋማት የሚውል የኃይል አቅርቦትን ተደራሽ ለማድረግ በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ የተቀናጀ አሰራር የሚተገበር ነው፡፡

በቀጣይም የታዳሽ ኃይል ምርቶች ስርጭት ላልተዳ ረሰባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች በቅንጅት የሚተገበረው የኤሌክትሪክ መስመር የመብራት አገልግሎት ኢኮኖሚያዊ ከማቅረብ በዘለል የዜጎችን የኑሮ ሁኔታ እና ተጠቃሚነት



አቶ ጌታቸው ዋቄ



አቶ ጎሳዬ መንግሥቴ

ለማረጋገጥ የሚያግዝ ነው፡፡

ባንኮች ለዚህ ፕሮጀክት ትግበራና ስኬት ቁልፍ ሚና እንዳላቸው ጠቅሰው፤ በተጨማሪ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ላለፉት 10 ዓመታት ሲተገብሩት እንደነበረው ከባንኩ የሚቀርበውን የብድር ገንዘብ በመጠቀም ለገጠሩ ማህበረሰብ የኃይል አቅርቦቱን ለማዳረስ የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡም አሳስበዋል።

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴርን በመወከል መልእክት ያስተላለፉት አቶ ጎሳዬ መንግሥቴ በበኩላቸው፤ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የብሔራዊ ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮግራም ትግበራን በዋናነት በመምራትና በማስተባበር ላይ ይገኛል ብለዋል፡፡

ከኢትዮጵያ መንግሥትና ከዓለም ባንክ በተገኘ የፋይናንስ ምንጭ ያልተማከለ የኤሌክትሪክና መብራት አቅርቦት ፕሮጀክት እ.አ.አ. ከ2021 ጀምሮ እየተተገበረ መሆኑን አስታውሰዋል።

የፕሮጀክቱ ዓላማ በመላው ሀገሪቱ በቤተሰብ፣ በማህበራዊ ተቋማትና በንግድ ድርጅቶች አስተማማኝ የኤሌክትሪክ ተደራሽነትን ማስፋፋት ነው ሲሉ አስረድተዋል።

እስካሁን ድረስ ከ56 ሚሊዮን በላይ ሕዝባችን ገና ኤሌክትሪክ አላገኘም ያሉት አቶ ጎሳዬ፤ የዚህ ፕሮግራም መጀመር የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተደራሽነትን በማስፋት ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት አመላክተዋል።

ያልተማከለ የኤሌክትሪክና መብራት አቅርቦት ፕሮጀክት በጥቅሉ አምስት ክፍሎች እንዳሉት ያስረዱት አቶ ጎሳዬ፤ በትናንትናው ዕለት የተጀመረው የዚህ ፕሮጀክት አካል የሆነው የ42 ሚሊዮን ዶላር ፕሮጀክት (ኮምፖነንት 3ነጥብ 2) 750 ሺህ ለሚደርሱ በገጠር ለሚኖሩ አባወራና እማወራዎች በፀሐይ ኃይል የሚሰራ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማቅረብ እንደሚያስችል ገልጸዋል።

ዜጎችን የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ማድረግ የሁሉንም አካላት ትብብር የሚጠይቅ መሆኑን አስታውሰው፤ ባለድርሻዎች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ በመወጣት ማህበረሰቡን ከጨለማ ለማውጣት የሚደረገውን ሀገራዊ ጥረት እንዲያግዙ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

## ተመራቂዎች በሙያቸው ውጤታማ ሆኖ ለመቆየት በትብብር መሥራት ይኖርባቸዋል

### -ኮሌጁ 202 የሕክምና ባለሙያዎች አስመረቀ

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- ተመራቂዎች በሙያቸው ውጤታማ ሆኖ ለመቆየት ከተለያዩ የጤና ባለሙያዎች ጋር በትብብርና በመከባበር መሥራት እንደሚኖርባቸው የጤና ሚኒስትር ዴኤታ አየለ ተሾመ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

የካቲት 12 ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ በተለያዩ መስኮች ለሰባተኛ ዙር ያሰለጠናቸውን 202 የሕክምና ባለሙያዎች ትናንት በዓድዋ መታሰቢያ ሙዚየም አስመረቀ።

በምረቃ ሥነሥርዓቱ የተገኙት አየለ ተሾመ (ዶ/ር፤ ተመራቂዎች የሕክምና ሙያ በቡድን ሥራ ላይ የተመሠረተና ጥረትን የሚጠይቅ መሆኑን ተገንዝበው ከተለያዩ የጤና ባለሙያዎች ጋር በትብብርና በመከባበር መሥራት እንዳለባቸው አስገንዝበዋል።

ሀገር የምትሠራው በሕዝቧ ነው፤ ሕዝብ በሁሉም ዘርፍ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን ሁለንተናዊ ጤንነቱ የተሟላና የተጠበቀ ሊሆን ይገባል ያሉት ዶክተር አየለ፤ ሀብት ባጠረበትና ያልተሟሉ ነገሮች በበዙበት ሀገር መሥራት ፈተና የሚሆነውን ያህል በችግር ወቅት ለሀገር የሚከፈል ዋጋ ሁሉ ዕድለኝነት ነው ብለዋል፡፡

እንደ ዶክተር አየለ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ የእናቶችንና የሕፃናትን ሞት እንዲሁም የተላላፊ በሽታዎችን በመከላከል የተሻሉ ውጤቶችን በማስመዝገብ ላይ ትገኛለች። ኮሌጁ ካለው ዘርፈ ብዙ የፊር ቀዳጅነት አስተዋጽኦ ባሻገር ከምስረታው ጀምሮ ላለፉት በርካታ ዓመታት በጤናው ዘርፍ ስሙን በደማቅ ቀለም እየጻፈ የመጣ አንጋፋ ተቋም ነው፡፡



የየካቲት 12 ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ ዋና ፕሮቮስት ኤልያስ ተዋበ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ኮሌጁ 66 ጠቅላላ ሐኪሞችን ጨምሮ፣ በድህረ ምረቃ መርሀ ግብር፤ በኅብረተሰብ ጤና፣ በኅብረተሰብ ጤና አጠባበቅና በሥነ ተዋልዶ ጤና፣ በሕፃናት ጤና አጠባበቅ ስፔሻሊቲ፣ በጠቅላላ ቀዶ ሕክምና፣ በውስጥ ደዌ ስፔሻሊቲ፣ በማህጸንና ጽንስ ሕክምናና በሌሎችም በድምሩ 202 የሕክምና ባለሙያዎች ማስመረቁን ተናግረዋል፡፡

ተመራማሪዎቹ በሚገቡበት ተቋም ሁሉ የተሻለ አፈፃፀም በማስመዝገብ ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው የበኩላቸውን አሻራ በማሳረፍ የኮሌጁ አምባሳደሮች ሊሆኑ እንደሚገባ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

እንደ ዶክተር ኤልያስ ገለጻ፤ ኮሌጁ የአገልግሎት አሰጣጡንና የትምህርት መርሀ ግብሩን በማስፋት የጤና ባለሙያ አነስተኛ በሆነባቸው የሕክምና ዘርፎች ላይ ትኩረት አድርጓል።

የጤና ሥርዓቱን የተረዱ ባለሙያዎችን ለማፍራት የሚረዳውን የቀጣይ 10 ዓመታት ስትራቴጂካዊ እቅድ በማውጣት ወደትግበራ ምዕራፍ ገብቷል ብለዋል፡፡

በምረቃ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ የጤና ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር አየለ ተሾመ፣ የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ዮሐንስ ጫላ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ዘላለም ሙላቱ፤ የተመራቂ ቤተሰቦችና ሌሎች ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

## ከ2017 ጀምሮ ሁሉም የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የውጤት ውል ስምምነት ይፈርማሉ

**ሞገስ ተስፋና ሙሉቀን ታደገ**

ጅማ፡- ከ2017 ዓ.ም ጀምሮ ሁሉም የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር የውጤት ውል ስምምነት ይኖራቸዋል ሲሉ የትምህርት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ኮራ ጡሹኔ ገለጹ።

አቶ ኮራ ሰሞኑን በጅማ ዩኒቨርሲቲ በተዘጋጀው የምክክር መድረክ ላይ እንደገለጹት፤ ከሚቀጥለው ዓመት ጀምሮ ውጤታማነታቸውን ለማጎልበት ሁሉም የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር የውጤት ውል ስምምነት እንዲፈጽሙ ይደረጋል።

ከፍተኛ የትምህርት ተቋማቱ በቀጣይ በውሉ መሠረት ሥራ ቆጥረው ያቅዳሉ፣ ሠርተው ያሳውቃሉ ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ስለዚህ ማንኛውም ሰው ኃላፊነትን ሲቀበል ተጠያቂነትንም አብሮ የሚቀበል ይሆናል ብለዋል።

የከፍተኛ ትምህርት ለሀገር ግንባታ የሚያስፈልገውን የተማረ የሰው ኃይል በማፍራት ትልቅ ሚና እየተጫወቱ ቢሆንም ከታሰበው አንጻር ገና ብዙ ሥራ እንደሚቀራቸው አመላክተዋል።

እንደ አቶ ኮራ ገለጻ፤ በትምህርት ጥራት፣ በሥራ ፈጠራ፣ በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚ ከመፍጠር፣ ምርትና ምርታማነትን ከማሳደግ አኳያ የተሠራው ሥራ ገና ነው። ይህን ለማስተካከል የሚረዱ የሀገሪቱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣ የትምህርት ፍኖተ ካርታና የተለያዩ ሰነዶች ተዘጋጅተዋል።

የሰነዶቹ ዋና ማጠንጠኛ የትምህርት ሥርዓቱ ምን መሆን አለበት የሚል ሲሆን፤ የትምህርት አሰጣጡ ድግግሞሽ የሚበዛበት ነው፤ ሥራ ፈጣሪ ዜጋን እያፈራ አይደለም፤ ሀብትን በአግባቡ እየተጠቀመ አይደለም የሚሉና መሰል ችግሮችን የሚያመላክት ነው ብለዋል።

ስለሆነም የሪፎርም ሥራዎች መቀረጻቸውን ጠቁ መው፤ ከሪፎርሙ መካከል ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ ሆነው ሙሉ ኃላፊነትን ወስደው ተቋማቱን በሚገባውና በታለመላቸው ዓላማ እንዲመሩ ማድረግ ነው። ለዚህም የጅምር ሥራ ስላሉ ተጠናክረው ይቀጥላሉ ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ አቶ ኮራ ገለጻ፤ ዩኒቨርሲቲዎች በቁጥር 47 ቢደርሱም አብዛኞዎቹ ግን አሠራራቸው የመመሳሰል ባህሪ ይታይበታል። ችግሩን ለመፍታት በመስክ ልየታ መሠረት ተደራጅተው የምርምር፣ የአፕላይድ ሳይንስ ተቋማት፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ፣ "የኮምፕሬንሲቭ" የትምህርት ዩኒቨርሲቲ ተብለው ተከፍለዋል።

አደረጃጀታቸው በመስክና በተልዕኮ ተለይተው ሲደራጁ የሚፈለገውን ውጤት እንዲያስመዘግቡ በማሰብ ነው ሲሉ አቶ ኮራ ገልጸዋል።

ጥራትን ከማሻሻል፣ የትምህርት ተደራሽነትን ከማስፋት፣ ከፈጠራ አኳያ ቴክኖሎጂ ትልቅ ሚና አለው ያሉት አቶ ኮራ፤ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ቴክኖሎጂን በተገቢው መጠቀም አለባቸው ብለዋል። ለዚህ ደግሞ ዩኒቨርሲቲዎች የሚሰሩት ሥራ መለካት እንዳለበትና ማንኛውም ኃላፊና አመራር ለሥራ እቅድ በሚይዝበት ውል ገብቶ ተጠያቂነት እንደሚኖረው አስረድተዋል።

የጅማ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ጀማል አባፊጣ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተከታታይ፣ ሰፊና አስቸጋሪ በሆነ ነባራዊ ሁኔታ እያለፉ መሆኑን ጠቁመዋል። በተለይም የትምህርት ጥራት መጓደል፣ ከቴክኖሎጂ ጋር በሚፈለገው ልክ መጓዝ አለመቻል ፈተናዎች ናቸው። ዩኒቨርሲቲዎች ችግሮችን ለመቅረፍ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታውን በመረዳት ሊሠሩ ይገባል ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የጋራ ትርክት እየገነባን ኢትዮጵያን እናበልጽግ!

በኢትዮጵያ ለረጅም ዘመን የዘለቀው የትርክት ቅኝት፣ በአንድ በኩል ፍጹማዊ አንድነትን የሚሰብክ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ፍጹማዊ ልዩነትን የሚያቀነቅን ዋልታ ረገጥነት ተጫጭኖት የከረመ ነበር። በሚዛናዊነት ላይ ያልቆመው፣ በተንሸዋረረ የታሪክ እይታ የሚባዝነው የሀገራችን የተዛባ ትርክት በየጊዜው ለሚያጋጥሙን ችግሮቻችን ምንጭም ሆኖ ቆይቷል።

ኢትዮጵያውያን ከውጭ የተቃጡብንን ጦርነቶች በጋራ የመመከት ባህል ቢኖረንም፤ የውስጥ ችግሮቻችንን በውይይት የመፍታት ልምዱን አላዳበርንም። በመሆኑም በችግሮቻችን ላይ ተነጋግሮ መግባባትን ገንዘባችን ልናደርግ ይገባል፡፡ ይሄ ሲሆንና ከመጠላለፍ ይልቅ አብሮ መልማትን፣ ከመነቃቀፍ መተባበርን፣ ከመራራቅ መቀራረብን ምርጫችን ስናደርግ የወል ትርክታችን የተነሰነሰበትን አቧራ አራግፎ ይነሳል።

ከስሜታዊነት ይልቅ አስተዋይነትንና ሚዛናዊነትን፣ ከቂም በቀል ይልቅ ይቅር መባባልን፣ ባለፈ ትርክት ከመበላላት ይልቅ የነገን ታሪክ በጋራ መሥራትን፣ ጠብመንጃ ከመማዘዝ ይልቅ ለሰላም መንበርከክን ባህል ስናዳብር፣ የኅብረ-ብሔራዊነታችንን በረከት እንቋደሳለን።

ለእኛ ለኢትዮጵያውያን የብሔር፣ የሃይማኖት፣ የባህል ወዘተ. ብዝሃነቶች ፀጋዎቻችን ናቸው። የራሳችንን ማንነት አክብረን የሌሎችንም ማክበር ብቻ ሳይሆን፤ ማስከበር ሰብአዊ ግዴታችን መሆኑን በተግባር እያጎለበትን ስንሄድ ለሰው ልጆች ክብር ሲሉ ራሳቸውን መስዋዕት እንዳደረጉት አባት እናቶቻችን የአርበኝነትን ክብር እንጎናፀፋለን።

በታሪካችን ካለፍንባቸው በላይ ችግሮችን የተጋፈጡ ሀገሮች ትርክታቸውን በአዎንታ በመቃኘታቸው የሀገረ-መንግሥት ግንባታቸውን አጠናቀዋል። ትርክትን በአሉታዊነት የቃኙት ደግሞ ተበታትነዋል፣ ተገዳድለዋል፣ ከነበሩበት ገናና ታሪክ ቁልቁል ተፈጥፍጠዋል።

በዚህ መልኩ በኅብረ-ብሔራዊነትና በአዎንታ የተቃኘ የወል ትርክት የአንድን ሀገር ሕዝብን አብሮነት የሚያጠናክርና የጋራ ሀገራዊ ዓላማ ለመሰነቅ ትልቅ አስተዋጽኦ ያለውና የታሪክ ሁነቶችን ጭምር የሚያስተሳስር ነው። ምክንያቱም የወል ትርክት አብሮነትና አንድነትን የማጠናከር ፋይዳው የላቀ ነው፤ በንዑስ ትርክት ላይ አተኩሮ መሥራትና ጽንፍ የረገጠ ትርክት መያዝ ደግሞ የመለያየትና የመከፋፈል ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ይታመናል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፤ በተለያዩ መድረኮች ባስተላለፏቸው መልዕክቶች ኢትዮጵያዊያንን በጋራ ሊያስተሳስር የሚችልና አንድነትን የሚያጸና የጋራ የሆነ ታላቅ ትርክት ያስፈልጋል ማለታቸው ይታወሳል። እናም የወል ትርክትን በመገንባት ማለት፣ ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን ማጽናት፤ የጋራ ተጠቃሚነትና የሀገር ግንባታ መሠረቶችን ማኖር ማለት ነው፡፡ ወቅቱም እኛ (ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን) ከምንጊዜውም የበለጠ ይሄንን የምንሻበት ነው።

ወንድማማችነትን፣ እህትማማችነትን እና ኅብረ ብሔራዊነትን የሚያጎለብት፤ የብሔራዊነትና የአርበኝነት ክብርን የሚያጎናፅፍ አሰባሳቢውንና ታላቁን ሀገራዊ ትርክት ለመገንባት የተጀመረው እንቅስቃሴ የአንድ ወቅት አጀንዳ ሆኖ እንደ ዘበት የሚቀር እንዳይሆን ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

ትርክትን የምንገራው የመተሳሰብ፣ የመረዳዳት እና የመከባበር እሴቶቻችንን በማጎልበት ነው። ታላቁ ሀገራዊ ትርክት በቤተሰብ የምንነጋገረው፣ በትምህርት ቤት የምናስተምረው፣ በየሃይማኖት ተቋሞቻችን የምንሰብከው፣ በየሚዲያው የምናሰራጨው ሃሳብ ውጤት በመሆኑ ለአንድ አካል ብቻ የሚተው ሳይሆን የሁላችንንም ርብርብ የሚጠይቅ ነው።

አሰባሳቢውን ታላቁን ሀገራዊ ትርክት ከማስረጽ ባለፈ ይህ ትውልድ በላቡ መስዋዕትነት ታሪክ እየሠራ መሆኑን ትናንትን፣ ዛሬን እና ነገአችንን አስተሳስሮ የያዘው የታላቁ ትርክት ውጤት የሆነው የዓድዋ ዜሮ ዜሮ ሙዚየምን እና ታላቁ የዓባይ ግድባችንን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል።

የወል እውነት ላይ የተመሠረተና ብዝሃነትን ያከበረ ትርክት በመገንባት ሰላምን ማጽናትና የጋራ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ይገባል። ኢትዮጵያውያን ከፋፋይ ትርክቶችን በመተው በኅብረ-ብሄራዊ አንድነት ላይ የተመሠረተ የወል ትርክት በመገንባት ሰላምን ማጽናትና የጋራ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ይገባናል።

ከፋፋይ አጀንዳዎች ሰላም እንዳይጸና፣ ልዩነትና ተቃርኖ እንዲበረታ የሚያደርጉ በመሆናቸው ሕዝብንና ሀገርን ክፉኛ ይጎዳሉ። በመሆኑም ኢትዮጵያዊያን ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን የሚያጠናክር የወል እውነትን መሠረት አድርገን መሥራት ይገባናል።

ሐሰተኛ ትርክት በኢትዮጵያውያን መካከል ጥርጣሬና ግጭትን በመፍጠር ሀገር የሚያዳክም ነቀርሳ ነው። ብዝሃነትን ያከበረ የወል ትርክትን መገንባት ይገባናል የምንልበት ምክንያትም ይሄው ነው።

የተለያዩ የታሪክ አረዳዶችንና አገላለጾችን ለማቀራረብ ከታሪክ ምሁራን ጋር በትብብር መሥራት ይገባል። ፍጹም ጠቅላይነትም ፍጹም ነጣጣይነትም ለኢትዮጵያ የማይበጁ በመሆናቸው፤ ኅብረ-ብሔራዊነትን ያከበረ አሰባሳቢ መንገድን መምረጥና መከተል አስፈላጊ መሆኑን ለቅፅበትም መዘንጋት አይገባም።

ከታሪካችን፣ ከሕልሞቻችን፣ ከሀገራዊ ጥቅሞቻችንና ከእሴቶቻችን የሚመዘዝ የጋራ ማንነት ያለን በመሆኑ፤ ይህንን ማጠናከር ላይ መሥራት ተገቢ ነው። በመሆኑም ኢትዮጵያውያን በኅብረ ብሔራዊ አንድነት ያጌጠ የወል እውነት ላይ የተመሰረተ ሀገራዊ ትርክት በመገንባት የጋራ ሰላምንና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ መሥራት አለብን።

የወል እውነት ለሀገር በጋራ በመቆም መሥራትን የሚያጎለብት፤ ይሄም ሉዓላዊነትን፣ ሰላምና አንድነትን የሚያጸና በመሆኑ ለዚህ መልካም ዓላማ በጋራ እንሥራ፤ የጋራ ትርክት እየፈጠርንም የነገ የወል ታሪካችንን እውን እናድርግ!


**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ከዛሬው ችግር ባሻገር ለሚገለጹት የከተማዋ የልማት ሥራዎች

**ስምስም መንግሥቱ**

ጉዞአችን ከአራት ኪሎ ወደ ሜክሲኮ ነው፡፡ ከጎኔ የተቀመጡት አንድ የእድሜ ባለፀጋ የመንገዱን ግራና ቀኝ በአግራሞት ይቃኛሉ፡፡ የማናችንንም ትኩረት አልፈለጉም፡፡ አካባቢው አሁን ላይ ያለውን ይዘትና ቀድሞ የነበረውን ሁኔታ እያነፃፀሩ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ነበር የሚናገሩት፡፡ እኔ ግን በጆሮዬ ጨዋታቸውን እያደመጥኩ፤ ሃሳባቸው በውስጤ ከሚፈጥሩብኝ ጥያቄዎች ጋር እያገናዘብኩ ነበር የሰማኋቸው፡፡

እኚህ አዛውንት በአካባቢያቸው ላሉት ሰዎች ሲናገሩ ባደመጥኩት መሠረት፤ አሁን ሳይንስ ሙዚየም የተገነባበት አካባቢ የእህል ወፍጮ አገልግሎት የሚሰጥበት ቦታ ነበር፡፡ በወቅቱ ወፍጮ ቤቱ ለቤተ መንግሥቱ አገልግሎት እንዲሰጥ ነው የተተከለው፡፡ አካባቢው ከፊሉ ጫካ፤ ከፊሉ ደግሞ ሜዳ የነበረ ነው፡፡

ስለ ታሪኩ ለመረዳት ካለኝ ፍላጎት አኳያ ባደረግናቸው የሃሳብ ምልልሶች እንዳጫወቱኝ፤ እርሳቸው በዚህ አካባቢ ኳስ ለመጫወት ያዘወትሩ ነበር፡ ፡ ግርምት የፈጠረባቸውም የዛኔ የሚያውቁት ቦታ እና አሁን ላይ ያለው የአካባቢው ይዞታ ነበር፡፡ በእርሳቸው ዘመን በዚህ መልኩ ከፊሉ ሜዳ፣ ከፊሉ ጫካ ሆኖ የቤተመንግሥት ወፍጮ ቤት የነበረበት ቦታ ታዲያ በእኔ ዘመን የተወሰነ ለውጥ ነበረው፡፡

ምክንያቱም፣ ከሳይንስ ሙዚየም ጀምሮ አሁን ለፓርክ የለማውና ወዳጅነት ፓርክ ተብሎ የተሰየመው ሰፍራ፤ ፊትበር በመባል የሚታወቅ፤ ከጭቃ በተሠሩ ቤቶች ውስጥ ሰፊ ቁጥር ያለው ነዋሪ ነው የነበረበት፤ ፊትበር የሚባል ጉሊት(ገበያ) የነበረውም ነው፡፡

በስፍራው የነበሩት መኖሪያ ቤቶችም ጥቂት የሚባሉት ካልሆኑ በስተቀር የተጎሳቆሉ ነበሩ፡፡ ለእይታም ለመኖሪያም የሚስቡ አልነበሩም፡፡ ሆኖም ነዋሪውም አንዳንዱ ተወልዶ አድጎበት፣ አግብቶ፣ የልጅ ልጅም ያየበት ስለሆነ እንከኑ አይታየውም፡፡ ነገር ግን ለመኻል ከተማ ቅርብ በመሆናቸው፣ ቤተመንግሥት አካባቢ እንደመገኘታቸው መገኘታቸው መስህብ አልነበራቸውም፡፡

በተለይ አካባቢው ላይ መጠጥ ቤቶችም በስፋት ስለነበሩ ሁካታና ግርግሩ በዚያው ልክ ነው የነበረው፡፡ ሆኖም አሁን ላይ ሆኖ ሲታሰብ ጭንቅ ያለ ስሜት ያለው አካባቢ እንደሆነ ይሰማን እንደሆን እንጂ፤ በጊዜው ግን ከማህበረሰቡ ጋር የተዋሀደ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ በአካባቢው በስም የሚታወቁ ስጋ ቤቶችና ምግብ ቤቶች ብቻ አልነበሩም፤ ይልቁንም የሴተኛ አዳሪዎች ሰፈር ተብለው እንደመለያ የሚጠሩም ነበሩ፡፡ እናም ይህን አካባቢ ነው፣ እንኳን ለማያውቀው ለሚያውቀውም ትዝታው እስኪጠፋው ተለውጦ እኚህን አዛውንት ያስደመማቸው፡፡

እኚህ በሸገር የከተማ አውቶቡስ ውስጥ ያገኘኋቸው አዛውንት፤ አካባቢው ላይ የተገነቡት ሕንፃዎች የነማን እንደሆኑ ጭምር ነበር ታሪክ ሲነግሩኝ የነበረው፡፡ ለምሳሌ፣ አሁን ፒያሳ ጣይቱ ሆቴል ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የሚገኘው የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር አገልግሎት ይሰጥ የነበረው ስቴድየም አካባቢ ነበር፡፡ ከእኝህ ሰው ጋር በነበረን አጭር የጉዞ ቆይታ እነዚህንና ሌሎችንም በርካታ የከተማዋን ታሪኮች ለመስማት የቻልኩት፡፡

በዚህ ረገድ በአዲስ አበባ ከተማ የተለያየ ታሪክ ያላቸው በርከት ያሉ አካባቢዎች ተለውጠዋል። እየተለወጡም ነው፡፡ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ መኖሪያ ቤቶች ሳር ቤት እንደነበሩ፣ የትራንስፖርት አገልግሎቱም ፈረስና ጋሪ እንደነበር፤ ከተማዋ በሂደት እየተለወጠች አሁን የምትገኝበት ላይ እንደደረሰች ደግሞ በታሪክ አዋቂዎች በቃል ከሚነገረው በተጨማሪ፣ የታሪክ ሰነዶችና ድርሳናትም ያስረዳሉ፡፡

ሆኖም በከተሞች እድገትና ለውጥ ውስጥ የሚነሱ ሃሳቦች አልታጡም፡፡ በዚህ ረገድ ሁሉም ጊዜውንና ዘመኑን ማድነቁ፣ ለውጥም ሲኖር ለምን የሚል ጥያቄ ማንሳቱ አይቀሬ ነው፡፡ ከታሪክ ጋር በማያያዝ አንድ ከተማ ከየት ተነስቶ የት ደረሰ ብሎ ለማነፃፀር የሚያስችል ነገር መኖር አለበት የሚል ወገን አለ፡፡ ይህን ሃሳብ የሚያነሱ ሰዎች ሲያልፉና ሲያገድሙ የሚያዩትና የለመዱት አካባቢ ሳያዩት እንኳን በዓይነ ህሊናቸው መግለጽ ይችላሉ፡፡ ለአብነትም ከአራት ኪሎ እስከ ፒያሳ ባለው የሚታወሱ ብዙ ነገሮችን ማንሳት ይቻላል፡፡

ፖስታ ቤት፣ ጆሊባር፣ ሰባደረጃ፣ ራስመኮንን ድልድይ፣ ወደ ፒያሳ ሲሻገሩ ደግሞ ወርቅ ቤቶች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ በተለይ ደግሞ የፒያሳ ወርቅ ቤቶች ውበታቸው ፊትለፊታቸው እንጂ በጀርባቸው ያሉት መኖሪያ ቤቶች የተጎሳቆሉ ናቸው፡፡ ለየት የሚያደርገው ታሪክ ወርቅን የሚያክል ሀብት ባረጀ ሰፈር ውስጥ ያለስጋት ለረጅም ዓመት ግብይት መከናወኑ ነው፡፡

በሌላ በኩል፣ የተጎሳቆለ ከተማ በአዲስ መተካት እንዳለበት የሚያምን፣ አስታራቂ ሃሳብ የሚያቀርበው ወገን አካባቢው መለወጡን ይደግፋል፡፡ ነገር ግን የነበረውን ነገር የሚያስታውስ መኖር አለበት የሚል እምነት አለው፡፡ ማስታወሻው በስም ስያሜ፣ አለያም በፎቶግራፍ ሲሆን፤ አንዳንዱም እንደ ፋይዳው ታይቶ የቅርጽ ለውጥ ሳያመጣ ዘመኑን የሚመስል እድሳት ተደርጎለት ለታሪክ ምስክርነት ይኑር የሚል ነው፡፡

ከዚህ አኳያ ሲታይ መልሶ ማልማት ሥራው የሕዝብና የምሁራን ሃሳብ ወይንም አስተያየት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ረገድም መንግሥትን የሚወቅሱም አልጠፉም፡፡ ሊታወቅ የሚገባው በመንግሥት ተደጋግሞ የሚነሳው በተለይም ከአዲስ አበባ ከተማ ጋር በተያያዘ እንደስሟ ውብና ጽዱ ሆና እንድትታይ፣ በዓለም ካሉ አቻ ከተሞች ጋር የተመጣጠነ የከተማ ይዘት እንዲኖራት፣ ዓለም አቀፍ ኩነቶች የሚከናወኑባት በመሆኗ ጭምር ከተማዋን የሚመጥን የልማት ሥራ ያስፈልጋታል፡፡

ምክንያቱም በእቅድ(በፕላን) ያልተገነቡ ቤቶችና የንግድ ቦታዎች መኖር ለመንገድ መሠረተ ልማት አጠቃቀም አስቸጋሪ አድርገውታል፡፡ የእግረኛና የተሽከርካሪ መንገዶችን ለመለየት እንኳን ያልተቻለባቸው አካባቢዎች ተፈጥረዋል፡፡ በጥቅሉ ከእቅድና ከክትትል ውጪ በዘፈቀደ የተሠሩ ሥራዎች ደግሞ ከተማዋን ዥንጉርጉር አድርገዋታል፡፡

ከዚህ በተጓዳኝ የሕዝብ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሆኑም በከተማዋ መሠረተ ልማቶች ላይ የሚፈጥረው ጫና አለ፡፡ ይሄን ጫና ለመቀነስ ደግሞ ዘመኑ የሚጠይቀውን የእድገት መንገድ መከተል ይጠበቃል፡፡ ይሄንን በማድረግ ሂደት የሚነሱ ቅሬታዎች እና የሚፈጠሩ ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ፤ ሆኖም ከችግሮቹ ባሻገር ያለውን ተስፋ እና የተሻለ ነገር መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡

ለምሳሌ፣ ከመንገድ መሠረተ ልማት ጋር ያለውን ማንሳት ይቻላል፡፡ አሁን ላይ አራት ኪሎ አካባቢ እየተከናወነ ያለው የመንገድ ማስፋት ሥራ ከመጀመሩ ከጥቂት ጊዜያት በፊት የመንገድ ጠርዝ ሥራ ተከናውኖ ነበር፡፡ ብዙም ሳይቆይ ደግሞ ቴራዞ ለማንጠፍ ጠርዙ ተነስቶ ጠጠር እንዲለብስ ተደረገ፡፡ ጠጠሩ እንደለበሰ ደግሞ መንገዱን የማስፋት አዲስ ሥራ ተጀመረ። ይሄን መሰል ሥራ በአካባቢው እንቅስቃሴ ላይም ሆነ ለሥራ በሚውል ሀብት ላይ የሚያሳድረው ጫናና የሚፈጥረው የሀብት ብክነት አለ፡፡

በመሆኑም እንዲህ ዓይነት ከተማዋን የማስዋብ፣ ለነዋሪዎች ምቹ የማድረግና ስሟን የሚመጥን ገጽታን የማላበሱ ተግባር የሚበረታታ እና ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባው ቢሆንም፤ እንዲህ ዓይነት ሥራዎች ሲታሰቡ እንደ መብራት፣ ውሃ፣ ስልክና ሌሎችም የኅብረተሰብ መገልገያዎች እንዳይስተጓጎሉ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ፤ እንዲሁም በተደጋጋሚ የዲዛይን ለውጥ ምክንያት የሚፈጠርን የሀብት ብክነት ማስቀረት የሚያስችሉ ተግባራት ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል።

ኅብረተሰቡም ሥራዎቹ ከዛሬ ችግር ባሻገር ያላቸውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ በመገንዘብ ለጊዜያዊ ችግር ራሱን ከማስገዛት ይልቅ ሥራዎቹ ፈጥነው እንዲጠናቀቁ የአጋዥነት ሚናውን ሊወጣ ይገባል፡፡ ምክንያቱም እነዚህ የልማት ሥራዎች ዛሬ ላይ ተቸግሮ ነገን የተሻለ ኑሮ፣ የተመቸ የኑሮ ከባቢን እውን ማድረጊያዎቻችን ናቸው፡፡

ዜና

# “የመንገድ ግንባታው በመጓተቱ ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውስ ተዳርገናል”

-የከምባታ ዞን ነዋሪዎች

# “መንገዱን በቀጣይ ዓመት ለተሽከርካሪ ክፍት ለማድረግ ታቅዷል”

-የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር

ክብረአብ በላቸው እና ማህሌት ብዙነህ

አዲስ አበባ፡- ሦስት ዞኖችን የሚያስተሳስረው የሃላባ-አንጋጫ-ዋቶና ዳምቦያ-ዱራሜ የአስፋልት የመንገድ ግንባታ በመጓተቱ ለችግር መጋለጣቸውን የከምባታ ዞን ነዋሪዎች ቅሬታ አቀረቡ።

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር በበኩሉ ግንባታውን 80 በመቶ በማድረስ መንገዱን በቀጣይ ዓመት ለተሽከርካሪ ክፍት ለማድረግ ማቀዱን አስታውቋል።

የከምባታ ዞን ነዋሪና የአንገጫ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል ሜዲካል ዳይሬክተር የሆኑት ፀደቀ ሶማኖ (ዶ/ር) ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የመንገድ ግንባታው በመጓተቱ በበጋ በከፍተኛ አቧራ ምክንያት ለዓይንና ለቆዳ በሽታዎች እየተጋለጠ ሲሆን፤ በክረምት ደግሞ በጭቃ ምክንያት ሕዝቡ የትራንስፖርት አማራጭ ማግኘት አልቻለም።

በተጨማሪም በመንገዱ መቆፋፈር ምክንያት ዝናብ ከዘነበ አምቡላንስ እንኳን መንቀሳቀስ ስለማይችል በወሊድ እናቶች ለከፍተኛ ስቃይና እንግልት ብሎም የሕክምና ፈላጊዎች የሰው ሕይወት እያለፈ መሆኑን ተናግረዋል።

መንገዱ በመጓተቱ ቀድሞ ለአጭር ርቀት ትራንስፖርት 20 ብር ይከፈል የነበረው አሁን ላይ እስከ 150 ብር የሚያስከፍል በመሆኑ ኅብረተሰቡ ላይ ኢኮኖሚያዊ ጫና እያሳደረ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

የአካባቢው አርሶአደር አቶ ሙላቱ ካሳ በበኩላቸው፤ መንገዱ በአሁኑ ወቅት ተቆፋፍሮ የተተወ በመሆኑ ያመረትኩትን ምርት በትራንስፖርት በማጓጓዝ ወደ ከተማ ወስጄ ለገበያ ማቅረብ የማይታሰብ ሆኗል ብለዋል፡፡

መንገዱ ከመበላሸቱ የተነሳ ለጭነት አገልግሎት የጋማ ከብት እንጂ ተሽከርካሪ መጠቀም የማይታሰብ መሆኑን ገልጸው፤ እርሳቸውም ምርታቸውን ለማጓጓዝ ከፍተኛ የትራንስፖርት ወጪ በመጠየቃቸው ለኪሳራ እየተዳረጉ መሆኑን በምሬት ተናግረዋል።

መንገዱ ገደላማ በመሆኑ ዝናብ ከዘነበ ሁለትና ሦስት ቀናትን መንገድ ላይ ለማደር እንደሚገደዱ የሚናገረው ሌላኛው አስተያየት ሰጪ፤ አይሱዙ የተሰኘውን የጭነት መኪና የሚያሽከረክረው ወጣት መክብብ ደስታ ነው።

የመንገድ ግንባታው ተለዋጭ መንገድ ሳይዘጋጅ ወደ ሥራ መገባቱ ያለውን ሁኔታ ከባድ እንዳደረገው የሚናገረው አሽከርካሪው፤ በዚህ ምክንያት በተሽከርካሪዎች ላይ በሚደርሰው ብልሽት ለከፍተኛ ወጪ እየተዳረጉ መሆኑን ገልጿል።

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የሶዶ ዙሪያ ፕሮጀክቶች ማናጀር ኢንጂነር ሰለሞን ሞላ በበኩላቸው በሰጡት ምላሽ፤ ከሀላባ-አንጋጫ-ዋቶና ዳንቦያ-ዱራሜ የሚገነባው መንገድ መጓተቱን አምነዋል፡፡

የዝግጅት ምዕራፍ ላይ የሥራ ተቋራጩ አስፈላጊውን ግብአቶችንና ማሽኖችን አዘጋጅቶ አለመምጣቱ፣ ሥራው ከተጀመረ በኋላ የነበረው የአቅም ውስንነትና የወሰን ማስከበር ሥራ ዋነኛ ምክንያቶች መሆናቸውን አስረድተዋል።

የመንገድ ግንባታው አሁን ላይ 18 በመቶ የተከናወነ ሲሆን፤ በሚቀጥለው ዓመት 80 በመቶውን ግንባታ በማጠናቀቅ ለትራፊክ ክፍት ለማድረግ መታቀዱን ኢንጂነር ሰለሞን አስታውቀዋል፡፡

ፕሮጀክቱ የዱራሜ ፣ደንቦያ ፣አንጋጫና ሀላባ ከተሞችን የሚያገናኝ መሆኑን ጠቁመው፤ መንገዱ ከሚሸፍነው 65 ኪ.ሜ ውስጥ 20 ኪ.ሜ የሚሆነው በከተሞቹ የሚገኝ በመሆኑ የወሰን ማስከበር ሥራውን ፈታኝ እንዳደረገው ተናግረዋል።

በተጨማሪም የግብዓት አቅርቦት፣ የዋጋ ጭማሪና በከተሞች አዲስ አወቃቀር ምክንያት የዲዛይን ለውጥ ማስፈለጉ ሌላው በግንባታ ሂደት ላይ ያጋጠመ ተግዳሮት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ፕሮጀክቱ ከተጀመረ ሦስት ዓመታትን ማስቆጠሩን አስታውሰው፤ የሥራ ተቋራጩን አቅም ውስንነት ለመፍታት ሰፊ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን አመላክተዋል።

በተለይም የጠጠር መፍጫና አስፓልት ግንባታ ማቡኪያ ማሽኖች እንዲተከሉ እንዲሁም ከድንጋይና አፈር ግብዓት ጋር በተያያዘ በከም

ባታ እና ሀላባ ዙሪያ ከ13 ሄክታር በላይ መሬት በመረከብ ኮንትራክተሩ እንዲያመርት የማድረግ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

መንገዱን በሥራ ተቋራጭነት የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን እያከናወነው ሲሆን፤ ባለስልጣኑ በየጊዜው ድጋፍና ክትትል በማድረግና የሚታዩ የአሠራር ክፍተቶችን በመፍታት በተሻለ ፍጥነት እንዲጠናቀቅ ይሠራል ብለዋል፡፡

በጉዳዩ ዙሪያ ኢፕድ ከተቋራጩ ከኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ስለግንባታው መረጃ ለማግኘት ጥረት ቢያደርግም ምላሽ ማግኘት አልተቻለም፡፡

65 ነጥብ 1 ኪሎ ሜትር የሚረዝመው የሃላባ፣ ከምባታ እና ሃዲያ ዞኖችን የሚያስተሳስረው የመንገድ ፕሮጀክት በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደርና በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን መካከል በተገባው ውል መሠረት በአንድ ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር በጀት ታኅሣሥ 2013 ዓ.ም ግንባታው መጀመሩ የሚታወስ ነው።

## “ከስምምነቱ በኋላ በትግራይ ሰፊ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ለመሥራት ቁርጠኛ መሆናቸውን ተናግረዋል። ከመንግሥት ጋር ለሚከናወኑ የጋራ ሥራዎች ከማህበረሰቡ በኩል ሰፊ ትብብር እንደሚያስፈልግ አመላክተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ልማትን በሚመለከት እንደተናገሩት፤ አዲስ አበባ ላይ የታየው ልማት ሌሎች ክልሎች ላይ እንዲደገም የተነሳው ጥያቄ ተገቢ እንደሆነ በመግለፅ፤ ትግራይም ይሁን አዲስ አበባ የሚለማው በሰዎች ጥረት በመሆኑ ሁሉም ልቡ ከተቀራረበና ከተወያየ ዕድገት ማምጣት የሚቻልበት መንገድ ቀላል ነው ሲሉ ተናግረዋል።

የገረዓልታ የገበታ ለትውልድ ሥራ በክልሉ እንደተጀመረ በማስታወስ፤ ሰላም በመኖሩ ይህ ዕድል ሊገኝ እንደቻለና ወደፊትም ሰላምና ውይይቶችን አጠናክሮ መቀጠል ከተቻለ በትግራይ ተጨማሪ የልማት ሥራዎችን ማከናወን እንደሚቻል አስታውቀዋል።

ተፈናቃዮችን በሚመለከት ባነሱት ሃሳብ፤ ሰው ከቦታው ተፈናቅሎ ሲኖር እጅግ ከባድ እንደሆነ በመጥቀስ፤ ኮሚቴ ተቋቁሞ ሁሉም ተፈናቃዮች ወደ ቀያቸው እንዲመለሱ ይደረጋል ብለዋል።

ኅብረተሰቡ ወደ ቤቱ ከተመለሰ በኋላ ያስተዳድረኛል የሚለውን ሰው ከራሱ ይምረጥ፤ ከዚያም ከተረጋጋ በኋላ ማንነቱን በሪፈረንደም ይመርጣል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የመጀመሪያው ጉዳይ ግን ቤቱን እንዲያገኝና እርሻውን እንዲያከናውን ማድረግ በመሆኑ መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ አስረድተዋል።

መንግሥት ምግብ፣ መድኃኒት፣ ማዳበሪያ፣ ትራክተርና ሌሎች አስፈላጊ ድጋፎችን እያደረገ መሆኑን ጠቁመው፤ ሌላው ኢትዮጵያዊ ጠግቦ እያደረ ትግራይ እንዲራብ አይፈለግም ሲሉ ተናግረዋል።

ከፕሪቶሪያው ስምምነት በኋላ መንግሥት በካሽ 45 ቢሊዮን ብር በቁሳቁስ ደግሞ 19 ቢሊዮን ብር ድጋፍ ማድረጉን አመላክተው፤ የኢትዮጵያ አቅም ማነስ እንጂ ከዚህም በላይ ድጋፍ የማድረግ ፍላጎት አለን ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በትምህርት፣ በጤናና በሌሎች በመሠረተ ልማቶችም አቅም በፈቀደው መልኩ መንግሥት እያገዘ እንደሆነ በመጥቀስ፤ በትብብርና በምክክር ላይ በተመሠረተ አግባብ በጋራ መሥራት የሚቻልባቸውን ጉዳዮች አጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፈዋል።

በክልሉ የሚያጋጥመው አብዛኛው ችግር ጊዜ ቢወስድም ሊፈታ የሚችል መሆኑን ተናግረው፤ ትግራይን ዳግም ለማነፅ ባለሀብቶችን በማስተባበር ቴሌቶን የማሰባሰብ ሥራ እንዲሠራ ጠቁመዋል።

የትግራይ ወጣቶችና ባለሀብቶችን በማቀናጀት ከፍተኛ የልማት ሥራ በክልሉ ሊሠራ እንደሚችል በመጠቆም፤ ለዚህም የትግራይ ባለሀብቶች ልማት ላይ ቀዳሚ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ እንደሚገባ አመላክተዋል።

ሰላም ካለ ዋናው ነገር ሥራ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ጠንክሮ ለመሥራት ደግሞ አላስፈላጊ ፖለቲካን መተውና ሠርቶ ማሳየት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

ከተሳታፊዎች ለተነሱት የተለያዩ ጥያቄዎች በተለይ የሀገር ባለውለታዎች ጡረተኞችን ደመወዝ ጉዳይ በተመለከተ ከክልሉ ጊዜያዊ አስተዳደር ፕሬዚዳንት ከአቶ ጌታቸው ረዳ ጋር ውይይት እንደሚያደርጉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስረድተዋል፡፡

## ሕዝባዊ ውይይቶቹ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በውስጡ ያለውን ውጥረት እንዲያረግብ፣ የጋራ መግባባት እንዲፈጠርና በሰላም አብሮ የመኖር እሴትን በማጎልበት ለሀገር ግንባታ መሠረት የሚጥሉ ናቸው ብለዋል።

በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች እና በክልሎች ከ70 ባላነሱ ዋናዋና ከተሞች ሕዝባዊ የውይይቶች መድረኮች መካሄዳቸውን አስታውሰው፤ የአንዱ ክልል አመራር ወደ ሌሎች ክልል ከተሞች በመመደብ ከፌዴራል ከፍተኛ አመራሮች ጋር በቅንጅት የተካሄዱ ውይይቶች መሆናቸውን አንስተዋል።

በውይይቱ ሕዝቡ ከመንግሥት ጋር በጋራ ጉዳዮች ለመወያየት የነበረው ፍላጎትና ቁርጠኝነት፣ ጥያቄዎቹን ሚዛናዊና ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ያነሳበት፣ የተሠሩ ሥራዎችን እውቅና የሰጠበትና ቀጣይነት እንዲኖራቸው ፍላጎቱን የገለጸበት፣ ጉድለቶችንም መንግሥት እንዲያርም በነፃነት ስሜት ያነሳበት እንደነበር አስገንዝበዋል።

አሳታፊና አካታች የውይይት መድረኮች ህብረ ብሔራዊ አንድነትን፣ ወንድማማችነትንና ትብብርን በማጎልበት በኅብረተሰብ ውስጥ ባሉ የተለያዩ ቡድኖች መካከል መተማመንን እንደሚያበረታም አብራርተዋል።

ከፍተኛ አመራሩም የሕዝቡን የማልማት ጥያቄ የተገነዘበበት ብሎም አንዱ የሌላውን አካባቢ ችግሮችና ሕመሞች መገንዘብ እንዲችል እድል ያገኙበት እና ተገቢው ልምድና ግንዛቤ ተፈጥሮለታል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ኅብረተሰቡ ከሰላምና መረጋጋት፣ ከኑሮ ውድነት የሥራ እድል ፈጠራ፣ የመሠረተ ልማቶች አቅርቦቶች በተለይም የንጽህ መጠጥ ውሃ፣ የኤሌክትሪክ ፣ መንገድ እና ቴሌኮም አገልግሎት አቅርቦትና ሌሎች የልማት ሥራዎች እና አካባቢያዊ ጉዳዮችን በስፋት ያነሳበት፣ በተነሱ ጉዳዮችና ችግሮች አፈታት ማን ምን መሥራት እንዳለበት የጋራ መግባባት እንደተፈጠረ ጠቁመዋል።

ከልማት አኳያ የተነሱ ጉዳዮች በጥቅሉ በሦስት ተከፍሎ ሊታዩ የሚችሉ ናቸው ያሉት ሚኒስትሩ፤ የመጀመሪያው በዕቅድ የተያዙ፣ በቂ በጀት የተመደበላቸውና በአስተዳደራዊ ችግሮች ምክንያት በወጉ ያልተፈጸሙ ናቸው፡፡ የእነዚህን መሠረታዊ ችግሮች ለይቶ በፍጥነት መፍታት ይገባል ብለዋል፡፡

ሁለተኛው በዕቅድ ያተያዙ ነገር ግን በበጀት እጥረት ምክንያት ያልተፈፀሙ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ኅብረተሰቡን በማስተባበር፣ ከአጋር አካላት ሀብት በማፈላለግ እና ልዩ ልዩ የፈጠራ መንገዶችን በመጠቀም መፍታት እንደሚገባ አመላክተዋል።

ሦስተኛው በእቅድ ያልተያዙ፣ ሰፊ ሀብትና ጊዜ የሚጠይቁ በፍጥነት ለመበልጸግ ከመፈለግ የተነሱ ጉዳዮች መሆናቸውን ገልጸው፤ እነዚህን በመካከለኛና የረጅም ጊዜ እቅድ ውስጥ በማካተት በቅደም ተከተል መፍታት እንደሚጠይቅ ተናግረዋል።

በአጠቃላይ ውይይቶቹ ኅብረተሰቡ የተጀመረውን ሁሉን አቀፍ ሪፎርም እና የለውጡን ሥርዓት ለማስቀጠል የበኩሉን ሚና በመወጣት ለሀገረ-መንግሥቱ ቀጣይነት ያለው ዝግጁነቱን እና ቁርጠኛ አቋም ያንጸባረቀበት መድረክ ነበር ብለዋል፡፡

እንዲህ ዓይነቶቹ መድረኮች በቀጣይም ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለባቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከተለያዩ ክልሎች ከተውጣጡ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር በበርካታ መድረኮች ባደረጉት ውይይት ማረጋገጣቸውን ዶክተር ለገሰ አንስተዋል።

## ኮሚሽኑ የሁሉንም...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እስካሁንም በሀገሪቱ ያሉትን ወረዳዎች በማዳረስ ከ90 ሺ በላይ ተሳታፊዎችን ማግኘት ችለናል ያሉት ዋና ሰብሳቢው፤ ለዋናው የምክክር መድረክ የሚቀርቡ አጀንዳዎችን በማሰባሰብ ረገድ ሁሉንም ተደራሽ ለማድረግ የሚሠራ ይሆናል ብለዋል።

አጀንዳዎችን በየፈርጁ የማደራጀት ሥራ የሚከናወነውም ሙሉ ለሙሉ አንድ አይነት የሆኑትን በተደጋጋሚ እንዳይቀርቡ ለመለየት እንጂ ሃሳብ ለማስቀረት አይደለም ሲሉ አስረድተዋል።

አሁን ላይ በምክክሩ ተሳታፊ የሚሆኑ ፓርቲዎች 65 ቢደርሱም በቀጣይም ተጨማሪ ፓርቲዎች በምክክሩ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚደረገው ጥሪ እንደሚቀጥል አስገንዝበዋል።

የኮሚሽኑ ዓላማ በሕዝቦችና በመንግሥት መካከል ያለውን ግንኙነት በማሻሻል መተማመን የሰፈነበት የፖለቲካ ሥርዓት ለመፍጠር መሆኑን ተናግረዋል። በተጨማሪ ኢትዮጵያውያን በሙሉ በሀገራቸው ጉዳዮች ላይ በመምከርና በመሠረታዊ ነገሮች በመስማማት ለሀገረ መንግሥት ግንባታ የበኩላቸውን የሚወጡበትና የኢትዮጵያም የወደፊት እጣ ፈንታ የሚወሰንበት ነው ብለዋል።

በመሆኑም በምክክሩ ሳይወከል የሚቀር ቢኖር ዓላማውን ለማሳካት የማይቻልበት ሁኔታ ይፈጠራል ያሉት ፕሮፌሰር መስፍን፣ በመሆኑም ካለምንም ገደብ ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል እንዲሳተፍ እንደሚሠራ አስታውቀዋል።

ከምክክር መድረኩ ተሳታፊዎች ከፀጥታ ጋር በተያያዘ በአግባቡ እየተወከሉም፤ እየተሳተፉም ያልሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች አሉ ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ ኮሚሽነሩ በሰጡት ምላሽ፤ ኮሚሽኑ የተቋቋመው በችግር ውስጥም ሆኖ ሀገራዊ ስምምነትን ለመፍጠር መሆኑን አንስተዋል።

ኮሚሽኑ ሲቋቋም ትግራይ ውስጥ ሰላም እንዳልነበረ አስታውሰው፤ ነገር ግን ዛሬ ክልሉ ሰላም በመሆኑ ኮሚሽኑ ሥራውን እያከናወነ መሆኑንና በሌሎች ቦታዎችም በተመሳሳይ ሥራው እንደሚቀጥል ጠቁመዋል።

በተጨማሪ ኮሚሽኑ ወደ ሥራ ሲገባ ከደቡብ አፍሪካ፣ ሩዋንዳ፣ መካከለኛው ምሥራቅና ላቲን አሜሪካ ሀገራት ተሞክሮ መወሰዱን አስታውሰው፤ አንዳንዶቹ ሀገራት በጦርነትና ባልተረጋጋ ሁኔታ ውስጥም ሆነው ምክር ያካሄዱበት ሁኔታ መኖሩን አመላክተዋል።

በኢትዮጵያም በተመሳሳይ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች ያሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች ያለውን ሁኔታ በመጠቀም ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚሠራ ይሆናል ብለዋል። በጉባኤው ከ12ቱ ክልሎችና ሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች የተወከሉ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፈውበታል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## ከዓባይ ግድብ 13ኛ ዓመት ባሻገር ፤

(ከመጋቢት 06/2016 ዓ.ም ነጻ ሃሳብ የቀጠለ)

የተለያዩ ቆየት ያሉ የጥናትና የምርምር ወረቀቶች መሠረት ሀገራችን ኢትዮጵያ በመስኖ መልማት ከሚችለው መሬት ውስጥ ግማሽ ያህሉ የሚገኘው በዓባይ ተፋሰስ ውስጥ ነው። የሚያስቆጨው ደግሞ እስካሁን የለማው ከ6 በመቶ አለመብለጡ ነው። እንደሚታወቀው የሀገራችን ግብርና የዝናብ ጥገኛ ነው። ኢትዮጵያም የአፍሪካ የውሃ ማማ በመባል ብትታወቅም፤ በየዓመቱ ሊባል በሚችል ሁኔታ በድርቅ እየተጠቃች ነው።

በተለይ በየአስር ዓመቱ ይከሰት የነበረው ድርቅ በበልግና በመኸር በዓመት ሁለት ጊዜ ሲጎበኘን እየተመለከትን ነው። በዚህ ያልተስተካከለና የሚቆራረጥ ዝናብ ምክንያት የሚከሰት ድርቅ ደግሞ ሚሊዮኖች ለምግብ እጥረት እንዲዳረጉ እያደረገ ነው ። ይሄ የሚሆነው ግን ኢትዮጵያ የዓባይ እናት ብትሆንም፣ ከግማሽ በላይ በመስኖ መልማት የሚችለው መሬቷ በዚሁ ተፋሰስ ቢገኝም፣ ወንዙን እና መሬቷን ለግብርና ልማት ሥራ ማዋል ሳትችል በመቆየቷ ነው።

ይሄን ላለማድረጓ የራስ ድክመት ካልሆነ በስተቀር፤ የዓባይ ወንዝን እንዳትጠቀም እንቅፋት የሚሆን ስምምነት ከማንም ጋር የላትም። በውሉ እንደሚታወቀውም ሀገራችን ከግብፅም ሆነ ከሱዳን ጋር የዓባይን ወንዝ በጋራ መጠቀም የሚያስችል ስምምነት እንኳን የላትም። ሆኖም ለዓባይ/ናይል ወንዝ 86 በመቶውን ውሃ የምታበረክተው ኢትዮጵያ፤ በ1929ኙም ሆነ በ1959ኙ የቅኝ ገዢ ስምምነት የማትገዛ/የማይመለከታት እንደመሆኑ ከ1950ዎቹ ጀምሮ በወንዙ ላይ የኃይል ማመንጫና የመስኖ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ለማድረግ ተደጋጋሚ ጥረት ስታደርግ ቆይታለች ።

እኤአ ከ1958 እስከ 1963 ድረስ አሜሪካ በኢትዮጵያ በኩል የዓባይን ወንዝ ለማልማት በሚደረጉ ጥረቶች ውስጥ ግንባር ቀደም ተዋናይ ነበረች። ጉዳዩ ዘላቂ ጥቅም እንጂ ዘላቂ ወዳጅ የለም እንዲሉ ሆኖ እንጂ፤ የዛሬውን ታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ጨምሮ 33 የመስኖና የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶችን በተለያዩ አከባቢዎች አጥንታ እንዲለሙ ምክረ ሀሳብ አቅርባ ነበር። ከእነዚህ ጥናቶች ሥራ ላይ የዋለው እኤአ በ1972 ዓ.ም የተገነባውና 128 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል የሚያመነጨው የፊንጫ የውኃ ኃይል ቀዳሚ ነው ማለት ይቻላል ።

ኢትዮጵያ በአንድ በኩል ድርቅ፣ በሌላ በኩል ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት ያለባት ሀገር ናት። ከዚህ አኳያ የውሃ ሀብቷን አልምታ መጠቀም አለባት። ለዚህም የመስኖ መሠረተ ልማትን በማስፋት እያደገ የመጣውን የሕዝብ ቁጥርና የምግብ ፍላጎቷን ለማጣጣም መትጋት፣ ሕዝቧን ከተመፅዋችነት ማላቀቅ ይጠበቅባታል። ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ ለምታደርገው ሽግግር፣ እንዲሁም በኩራዝ ጭስ ለሚጨናበሰው ከ60 ሚሊዮን ለሚበልጠው ሕዝቧ የኤሌክትሪክ ኃይልና መብራት ለማቅረብ እንደ ዓባይ ያሉ ዓመቱን ሙሉ የሚፈስሱ ወንዞቿን ገድባ መጠቀም የሞት ሽረት ትንቅንቅ እየሆነ መጥቷል ።

ኢትዮጵያ ወንዞቿን ተጠቅማ ልማቷን ከማፋጠን ባሻገር፤ ለተፋሰሱ ሀገራት የኃይል አማራጭ የመሆን እምቅ የተፈጥሮ ፀጋ አላት። ይሁንና እስከቅርብ ዓመታት ድረስ በድህነቷ እንዲሁም ከዓለማቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ብድርና ድጋፍ ለማግኘት የምታደርገው ጥረት በግብፅ የተቀናጀ ስውርና ይፋ ዲፕሎማሲያዊ ዘመቻ የተነሳ እቅዷ ሁሉ ይጨናገፍባት ስለነበር ግዙፍ የኃይል ማመንጫዎችንና ታላላቅ የመስኖ መሠረተ ልማት ግንባታዎችን ማካሄድ ሳትችል ቀርታለች። የሚያሳዝነው ለኢትዮጵያ ሲሆን የሚታጠፈው የዓለማቀፍ የፋይናንስ ተቋማት እጅ ለግብፅ ሲሆን ግን ያለስስት ይዘረጋል። ለጋስ ይሆናል ።

**ኢትዮጵያ በአንድ በኩል ድርቅ፣ በሌላ በኩል ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት ያለባት ሀገር ናት፡፡ ከዚህ አኳያ የውሃ ሀብቷን አልምታ መጠቀም አለባት፡፡ ለዚህም የመስኖ መሠረተ ልማትን በማስፋት እያደገ የመጣውን የሕዝብ ቁጥርና የምግብ ፍላጎቷን ለማጣጣም መትጋት፤ ሕዝቧን ከተመፅዋችነት ማላቀቅ ይጠበቅባታል**

ግብፅም ይህን በመጠቀም ኢኮኖሚዋን ማሳደግ ችላለች። በዚህም የሀገር ውስጥ ጥቅል ምርቷ 235 ቢሊዮን ዶላር ሲሆን ፤ የዜጎቿ የነፍስ ወከፍ ገቢ 2ሺህ 440 ዶላር ደርሷል። የኢትዮጵያ ጥቅል የሀገር ውስጥ ምርት ከ164 ቢሊዮን ዶላር በላይ ሲገመት፤ የነፍስ ወከፍ ገቢዋ ደግሞ ወደ 1500 ዶላር ይገመታል። ከዚህ የድህነት አረንቋ ወጥቶ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ የተፈጥሮ ሀብቷን በተለይ የውሃ ሀብቷን በአግባቡ ማልማት ይኖርባታል።

ኢትዮጵያ ዛሬ ላይ ያላት የሕዝብ ብዛት ከግብፅ ሕዝብ ቁጥር ስለመብለጡ ይነገራል። ይሄ ደግሞ የምግብና የኤሌክትሪክ ኃይል የሚያስፈልገው ሕዝብ ቁጥር እና ይሄን ለማሟላት መሥራት ያለበትን ሥራ ለመረዳት የሚያስችል ነው። እናም ከግብፅ በላይ የውሀ ሀብቷን ለመስኖና ለኃይል ማመንጫ መጠቀም ይኖርባታል ማለት ነው። በግዛቷ ስር ያለ የውሃ ሀብቷን መጠቀም ደግሞ ሉዓላዊ መብቷ ነው። ሆኖም የፋይናንስ እጥረትና የቴክኖሎጂ ውስንነት ዘርፉን ለማልማት የተያዘውን እቅድ ፈታኝ ቢያደርገውም ተጨማሪ የውሃ ኃይል ማመንጫዎችንና የመስኖ አውታሮችን መገንባት ቅድሚያ የተሰጠው ተግባር ሆኖ ይቀጥላል። ቁልፉም የእድገትና የልማት ግብ በአጭር ጊዜ ውስጥ በሁለንተናዊ መልኩ ድህነትን መቅረፍ ነው።

በ2003 ዓ.ም ከሱዳን ድንበር 40 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ግንባታው የተጀመረውና ለኃይል ማመንጫነት የሚውለው፣ 74 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ የሚይዘው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ እድገትንና ልማትን በማፋጠን ዜጎችን ከድህነት የማላቀቅ ራዕይን ሰንቋል ። ግድቡ በቀን እስከ 6ሺህ ሜጋ ዋት፣ በዓመት 15ሺህ 130 ጊጋ ዋት ኃይል የማመንጨት አቅም አለው። በዚህም የሀገር ውስጥ የኤሌክትሪክ ኃይል ፍላጎትን በማርካት ለምስራቅ አፍሪካ በተለይ ለራስጌ ተፋሰስ ሀገራትም የማቅረብ እቅድ አለው ።

ግድቡ በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኘውን የታዳሽ ኃይል ተደራሽነት ያሳድጋል። የዓለም ባንክ ጥናት እንደሚያመለክተው ከሰሐራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት የታዳሽ ኃይል ሽፋን ከ15 በመቶ በታች ሲሆን፣ የሀገራችን 3 ነጥብ 5 በመቶ፣ የሱዳን 41 ነጥብ 3 በመቶ፣ የግብፅ 97 ነጥብ 6 በመቶ ነው ከሰሐራ በታች ያሉ ሀገራት የኤሌክትሪክ ሽፋን 24 በመቶ፤ የኢትዮጵያ ከ45 በመቶ ያልበለጠ፣ የሱዳን ከ57 በመቶ ያልበለጠ ሲሆን፤ የግብፅ ሽፋን ግን 100 በመቶ ደርሷል ።

በዓባይ/ናይል ውሃ አጠቃቀም ላይ ግብፅ የቅኝ ግዛት ዘመን ስምምነቶችን በመጥቀስ ብቸኛ ባለመብትና ተጠቃሚ እኔነኝ በማለት የያዘችው ግትር አቋም የራስጌ ሀገራት በዓለማቀፍ ሕግ የተረጋገጠላቸውን ውሃውን በፍትሐዊነት የመጠቀም ተፈጥሯዊ መብት የሚጥስ ስለሆነ በንግግርና በውይይት ካልተፈታ ለግጭት ሊዳርግ ይችላል ተብሎ እየተፈራ ነው።

የዓባይ ወንዝ እርዝመት 6ሺህ 650 ኪሎ ሜትር ይጠጋል። የተጠቃሚው ሕዝብ ቁጥር አንድ ላይ ቢደመር ወደ አምስት መቶ ሚሊዮን ይደርሳል። ኢትዮጵያ እና ግብፅን በዲፕሎማሲው መስክ በተደጋጋሚ በጠረጴዛ ዙሪያ እንዲገናኙ እና እንዲነጋገሩ አድርጓል። ሆኖም ግብፅ የምታቀርበው ሀሳብ ሰጥቶ ለመቀበል ዝግጁ አለመሆኗን በተደጋጋሚ አሳይቷል። ግብፅ የህዳሴው ግድብ 40 ቢሊዮን ኪዩቢክ ውኃ በየዓመቱ ይልቀቅ በሚል ያቀረበችው ሐሳብ በአብነት ይወሳል። የኢትዮጵያ ወገን ተደራዳሪዎች ልዑካን መሪ አምባሳደር ስለሺ በቀለ ተቀባይነት የሌለው ጥያቄ መሆኑን በጊዜው ምላሽ ሰጥተዋል። የናይል ወንዝ ለኢትዮጵያ፤ ግብፅ እና ሱዳን የመኖር እና ያለመኖር ጥያቄ እንደኾነ በበርካታ ታዛቢዎች ይነገራል። እናም ሦስቱ ሃገራት ተገናኝተው ፍትሐዊ አጠቃቀም ላይ ቁጭ ብለው መነጋገር ይጠበቅባቸዋል ።

ግብጽ ባለፉት ዓመታት በኢትዮጵያ ከባዱ የክረምት ወቅት ሲጀምር እየጠበቀች ተፅዕኖ ማሳደር ይችላሉ በምትላቸው ሀገራትና ተቋማት በኩል በውሃ አጠቃቀሙ ዙሪያ አሳሪ ስምምነት እንዲደረግ ግፊት ስታደርግ ቆይታለች ። ግብፅና ሱዳን፣ ስምምነት ላይ ሳይደርሱ ኢትዮጵያ ግድቡን መሙላት አትችልም የሚል ተቃውሞና ማስፈራሪያቸውን ቢገፉበትም ኢትዮጵያ 4ኛውን ዙር የውሃ ሙሌት በስኬት አጠናቃለች። በግድቡ የተወዛገቡት ኢትዮጵያ ግብፅና ሱዳን ተከታታይ ድርድርና ውይይት ሲካሄዱ ቢቆዩም እስከአሁን ይህ ነው ከሚባል ስምምነት ላይ አልደረሱም።

ሱዳንና ግብፅ ሦስቱ ሀገራት በህዳሴው ግድብ ዙሪያ በሚያደርጉት ድርድር ከአፍሪካ ኅብረት ውጪ ሌሎች ሀገራትና ዓለማቀፋዊ ተቋማት እንዲሳተፉ በተደጋጋሚ ሲወተውቱ የቆዩ ሲሆን፤ ኢትዮጵያ ግን በአደራዳሪነት ከአፍሪካ ኅብረት ውጪ ማንንም እንደማትቀበል እና ሌሎች ዓለም አቀፍ ታዛቢዎች ግን ሊኖሩ እንደሚችሉ ስትገልጽ ቆይታለች በዚህም በአፍሪካ ኅብረት አደራዳሪነትና በዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ታዛቢነት ሲካሄድ የከረመው ድርድር ተጨባጭ ስምምነት ላይ መድረስ ሳይችል ቀርቷል። ኢትዮጵያ በህዳሴው ግድብ ድርድር ሰበብ የዓባይን ወንዝ ተጠቃሚነቷን የሚገድብ ስምምነት እንደማትቀበል በተደጋጋሚ ገልጻለች ።

ኢትዮጵያ በመስከረም ወር 2013 ዓ.ም የመጀመሪያ የግድቡን ሙሌት በማካሄዷ ሳቢያም የትራምፕ አስተዳደር ለሀገሪቱ ከሚሰጠው እርዳታ ላይ ቅነሳ እንደሚያደርግ በማስታወቅ ሀገሪቱ ከአሜሪካ ታገኝ የነበረውን የገንዘብ ድጋፍ ማስቀረቱ አይዘነጋም። በዚያው ዓመት ሰኔ ወር ላይ የተካሄደውን 2ኛውን ዙር የውሃ ሙሌት ተከትሎ ግብፅና ሱዳን በህዳሴው ግድብ ዙሪያ ለተከሰተው አለመግባባት በተመሳሳይ ጉዳይ ቀደም ሲል ባልታየ ሁኔታ ለተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት አቤቱታ አቅርበው፤ ምክር ቤቱ ሐምሌ 2013 ዓ.ም በጉዳዩ ላይ ለመምክር ተሰበስቦ ነበር።

ኢትዮጵያም በህዳሴው ግድብ ጉዳይ የፀጥታው ምክር ቤት መወያየቱን እንደማትቀበለው በማስታወቅ ጉዳዩ ቀደም ሲል በተያዘበት የአፍሪካ ኅብረት በኩል መቋጫ እንዲያገኝ ጠይቃለች። ይህ ጥያቄዋ ተቀባይነትን አግኝቶ ምክር ቤቱ ጉዳዩ በአፍሪካ ኅብረት በኩል ሊታይ ይገባል የሚል ውሳኔ ማሳለፉ አይረሳም። ሆኖም ከፍ ብሎ ለመግለጽ እንደተሞከረው ግብፅ ይሄን ሀሳብ ለመቀበል ዝግጁ አልሆነችም ።

### እንደ ማጠቃለያ

ለዓባይ/ናይል ወንዝ 86 በመቶ ውሃ የምትገብረው ኢትዮጵያ ፍትሐዊ በሆነ አግባብ ውሃውን የመጠቀም መብቷ ለድርድር የሚቀርብ ጉዳይ አይደለም። ይሁንና ግጭትንና አለመግባባትን ለመፍታት ሰባቱ የራስጌ የተፋሰስ ሀገራት የቅኝ ግዛት ዘመን ስምምነቶች ፍትሐዊ ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ አዳዲስ ውሎች ሊተኩ እንደሚገባ የሚጠይቀውና በ2002 ዓም የተፈረመውን የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት (Cooperation Framework Agreement / CFA) ሥራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል ።

ስምምነቱን የተፈራረሙ ሀገራት ብሩንዲ ኬኒያ፣ ዑጋንዳ፣ ኢትዮጵያ፣ ታንዛኒያና ሩዋንዳ ሲሆኑ የትብብር ማዕቀፉ የናይልን ወንዝ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ መጠቀምን የሚያረጋግጥና ዋስትና የሚሰጥ ቋሚ ኮሚሽን እንዲቋቋም የሚጠይቅም ነው። ዳሩ ግን ሱዳንና ግብፅ ይህን የትብብር ማዕቀፍ ለመፈረም ፈቃደኛ ባይሆኑም በ2007 ዓ.ም በግብፅ፣ በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል የተፈረመውን የመርሆዎች መግለጫ (Declaration of Principles) ፈርመዋል ።

በዚህ ስምምነት ሱዳንና ግብፅ የህዳሴ ግድብ ፕሮጀክትን የተቀበሉ ሲሆን ኢትዮጵያም ግድቡ በግርጌ ተፋሰስ ሀገራት ማለትም በግብፅና በሱዳን ሊያሳድረው የሚችል ተፅዕኖ ወይም ጉዳት ካለ ጥናት እንዲደረግ ተስማምታለች። በዚህ ስምምነት ላይ ተከታታይ ውይይቶች የተካሄዱ ሲሆን ተስፋም ተጥሎባቸው ነበር። የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ለቀጣናዊ ትብብር አብነት የሚሆንና የራስጌ ሀገራትን ተጠቃሚ የሚያደርግ ፕሮጀክት ስለሆነ ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ ድጋፍ ሊደረግለት ይገባል። ግብፅም በግድቡ ውሃ አሞላል ላይ ከኢትዮጵያ ጋር ጀምራ ወደነበረው ድርድር ብትመለስ ሀገራቱን ተጠቃሚ ማድረግ የሚችል መግባባት ላይ መድረስ ይችላል ።

ሻሎም ! አሜን ።

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# 39 ዓመታት በባቡር ቴክኒሺያንነት

እፀገነት አክሲሉ

አሁን አሁን መጠነኛ መሻሻሎች ያሉ ቢሆንም ቀደም ባለው ጊዜ ግን ሴቶች ከማጀት አልፈው ተምረው ትልቅ ደረጃ ደርሰው አደባባይ እንዲታዩ፤ ሠርተው ገቢ እንዲያገኙ የሚፈቅድ ማኅበረሰብ እምብዛም አልነበረም። ከዛ ይልቅ ሚስት፤ እህት፤ እናት ሆነው ቤታቸው ውስጥ ተወስነው እንዲቀመጡ ልጆቻቸውንና የትዳር አጋራቸውን እንዲሁም መላ ቤተሰባቸው መንከባከብ ሥራቸው እንዲሆን ነበር ያልተጻፈው በማኅበረሰቡ ልብ ውስጥ ያለው ሕግ የሚያዘው።

በዚህ ኃታች አስተሳሰብ ደግሞ ብዙዎች ወደ ሕልማቸው መድረስ ሳይችሉ ብዙ እምቅ ችሎታን ይዘው ቤታቸው እንዲቀመጡ ተገደዋል። በተቃራኒው ችግሮችን ኃታች ሁኔታዎችን ተቋቁመው አቅማቸውን አውጥተውና አትችሉም ለሚሏቸው ሁሉ መቻላቸውን በተግባር አሳይተው እጅን በአፍ ያስጫኑ ከራሳቸው አልፈው ለብዙዎች የእንጀራ በርን የከፈቱ በርካታ ሴቶችም አሉ።

ይህ በእንዲህ እያለ ግን የሴቶችን መብት ለማስከበር መብታቸውን ብቻ ሳይሆን በተለያዩ መስኮች ላይ እኩል ተሳታፊነታቸውን ለመጨመር መንግሥትን ጨምሮ በራሳቸው ተነሳሽነት ተቋማትን መሥርተው የሚንቀሳቀሱ ብዙ አካላት አሉ፤ ምናልባት እነዚህ ወገኖች በዘርፉ ምን ያህል ሠርተው ምን ውጤት አመጡ የሚለውን ለመመለስ ጥናት የሚፈልገው ቢሆንም ባለው ሁኔታ ግን ጥቂትም ቢሆን ተጨባጭ የሚባሉ ለውጦችን ማየታችን አልቀረም ።

ሴቶችን ማብቃት በትምህርታቸው እንዲሁም በሚፈልጓቸው ዘርፎች ተሰማርተው ውጤታማ ማድረግ ግን ለመንግሥት አልያም ለግብረሠናይ ድርጅቶች የሚተው ሳይሆን ሁላችንም ከቤታችን ጀምረን ልንሠራው እና ልንወጣው የሚገባ ኃላፊነት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

የዛሬ የሕይወት ገጽታ ዓምድ እንግዳችን ከወንዶች በላይ ብርቱና ጠንካራ ሴት ናቸው። ያሰቡበት ለመድረስ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ለ39 ዓመታት ከባድ የሚባለውን የባቡር ቴክኒሺያንነትን ሙያ የሠሩ ናቸው።

ወይዘሪት አማረች ቦጋለ ተወልደው ያደጉት በፍቅር ተምሳሌቷ በድሬዳዋ ከተማ ነው። እናትና አባታቸው ወንድም ሴትም ልጆች ያሏቸው ቢሆኑም በተለይ አባታቸው እሳቸውን ወንድ አድርገው ለማሳደግ ከፍ ያለ ፍላጎት ነበራቸው። በዚህም አማረች ውሎዋቸው ከወንድማቸው ጋር ሆነ፤ አባታቸውም እናታቸውም በዚህ ተቃውሞ አልነበራቸውም። ወንድማቸው የሚያደርጉትን ነገር ሁሉ ያደርጋሉ፤ እንደ ወንድማቸው ብርቱ ሠራተኛ ናቸው። በትምህርትም የሚታሙ አልነበሩም፤ ከሁሉም በላይ ግን አባታቸው "......የእኔ ልጅ ጀግና ነሽ ፤ምንም አያቅትሽም" እያሉ ያሳደጓቸው ጠንካራ ሴት ናቸው።

".....ትውልዴ ሁሉም በሚወዳት የፍቅር ተምሳሌት በሆነችው ድሬዳዋ ከተማ ለገሃሬ አካባቢ ሲሆን ያደግሁት ደግሞ ገንደቆሬ ቀበሌ ነው። ከአባትና ከእናቴ እንዲሁም ከእህት ወንድሞቼ ጋር ነው የኖርኩት" ይላሉ።

ወይዘሪት አማረች የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ድሬዳዋ ከተማ አቡነ እንድሪያስና ሚካኤል ትምህርት ቤት የተማሩ ሲሆን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ በድሬዳዋ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መከታተላቸውን ይናገራሉ።

ወይዘሪት አማረች በትምህርት የማይታሙ ብሎም ለራሳቸው የማያንሱ ነበሩ። ነገር ግን ወንዳወንድ ሆነው ማደጋቸው እሳቸውም የወንድማቸውን ፈለግ ለመከተል መመኘታቸውና በጠቅላላ ነገረ ሥራቸው ሁሉ የወንድ መሆኑ በትምህርታቸው ላይ ከፍ ያለ ደረጃ እንዳይደርሱ የድርሻውን የተወጣ ይመስላል ።

የአንደኛ ደረጃም ሆነ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ሆነው ለጓደኝነት የሚመርጧቸውም ወንዶች ነበሩ። ውሎዋቸውም ከወንዶች ጋር ነበር። ምንም እንኳን የሴት ጓደኞች ቢኖሯቸውም ልክ ከወንዶቹ ጋር ተስማምተው እንደሚኖሩት አይነት ግንኙነት አይፈጥሩም። በጠቅላላው እሳቸው የሚያደሉት ለሴታዊ ሳይሆን ለወንዳዊ ባሕርያቸው እንደነበር ይናገራሉ።

ድሬ ከምትታወቅበት ነገር አንዱና ግንባር ቀደሙ ባቡሯ ነው። ከአዲስ አበባ ተነስቶ ብዙ ኪሎ ሜትሮችን አቋርጦ በበረሃና በጫካ ውስጥ የሚያልፈው ባቡር ደግሞ ለድሬ መታወቂያዋ ከመሆኑም በላይ ብዙዎች ብዙ ትዝታ ያፈሩበት እንጀራ ፈጥሮ ብዙ አባወራዎችን ያኖረና በርካታ ቤተሰብ በሁለት እግሩ እንዲቆም ምክንያት የሆነ ስለመሆኑ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ የሚረዳው ነው።

አማረችም አባታቸው በምድር ባቡር ውስጥ ተቀጥረው ያገለግሉ ነበር። በወቅቱ እሳቸውም ሆኑ አባታቸው ሥራውን እንደ ገቢ ማግኛና ቤተሰብ ማስተዳደሪያ ያዩታል እንጂ ከትውልድ ትውልድ ይወራረሳል ብለው በፍጹም አላሰቡም ነበር። ነገር ግን የሕይወት አጋጣሚ ወዴት እንደሚወስድና ምን እንደሚፈጥር አይታወቅምና በአባታቸው የሚያውቁትን ምድር ባቡር እሳቸውም የእንጀራ ቤታቸው ያደርጉት ዘንድ እድሉን ማግኘታቸው አልቀረም ።

"......በማንኛውም መንገድና ሁኔታ እኔ ከወንድሜ ስር ጠፍቼ አላውቅም እሱ ያደረገውን ነገር ሁሉ አደርጋለሁ፤ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪም ሆኜ ብዙ ነገሬ እሱ ነበር፤ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ገብቼም አብዛኛው ነገሬ ከቀለሙ ትምህርት ይልቅ ለሙያ ትምህርት ትኩረት አደርግ ነበር" ይላሉ።

አማረች ከልጅነታቸው ጀምሮ ከወንድማቸው ጋር በመዋል የለመዷቸውን ኋላም በወንድማቸው አበረታችነት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ገብተው የብረታ ብረት ሥራ ትምህርት (ጂ ኤምን) ተማሩ።

".........ትምህርቱን እንደነገርኩሽ ከወንድሜ ተማክሬ እኔም ወድጄው የገባሁበት በመሆኑ ስማረው ምንም አልከበደኝም፤ እንደውም ከወንድ ልበልጥ ሁሉ እችላለሁ። የንድፈ ሃሳቡንም፤ የተግባሩንም ትምህርት በሚገባ በመማር በዲፕሎማ ለመመረቅ ችያለሁ" በማለት የትምህርት ቤት ቆይታቸውን ያስታውሳሉ።

አማረች ወንድማቸው በዚህ መልኩ ሲያግዟቸው እናትና ሌሎች የቤተሰባቸው አባላትም አልተቃወሟቸውም፤ ነገር ግን ሁለተኛ ደረጃን እየተማሩ ባለበት ወቅት ግን የትምህርት ቤቱ የደንብ ልብስ (ዩኒፎርም ) ለሴቶች ቀሚስ ለወንዶች ደግሞ ሱሪ ያዝ ስለነበር እሳቸው ደግሞ ቀሚስ ለብሰው አላደጉምና ሁኔታ በጣም ፈታኝ ሆነባቸው፤ ትምህርት ለማቋረጥ ሁሉ ፈልገው እንደነበር ያስታውሳሉ።

".......እኔ ቀደም ብዬም እንደነገርኩሽ አባቴ ሱሪ እያለበሰ በርቺ እያለ ወንዶች የሚያደርጉትን ነገር እንዳደርግ እየፈቀደልኝ እንደውም እያበረታታኝ ወንድሜም እንደዛው የሚሄድበት ሁሉ ይዞኝ እየሄደ ነው ያደኩት። ይህ ሁኔታ በአንደኛ ደረጃ የትምህርት ቤት ቆይታዬ ምንም አልረበሸኝም፤ ነገር ግን ወደሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ስገባ በተለይም የደንብ ልብስ ቀሚስ ልበሺ ስባል ነገሮች ከበዱኝ። እንደዛ ለብሼ ልማር እንደማልችል ለቤተሰቤም ለመምህራኖቼም አሳወኩ፤ ነገሩ በጣም ከባድ ቢሆንም ቤተሰቦቼ ትምህርት ቤቱን ነግረውልኝ ከሁሉም ሴቶች በተለየ እኔ ብቻ ሱሪ ለብሼ እንድገባ ተፈቅዶልኝ ነው የተማርኩት" ይላሉ።

አማረች ምድር ባቡር ላይ ይሠሩ የነበሩት አባታቸው በጡረታ ሲገለሉ ድርጅቱ ባለው አሠራር መሠረት አባታቸውን ተክተው ተቋሙን አራት ዓመት በተማሩት የብረት ሥራ ትምህርት ሊያገለግሉ ፈተና ተፈትነው በማለፋቸው ተቋሙን ስለመቀላቀላቸውም ነው የሚናገሩት።

እሳቸው የብረት ሥራ ሙያን ይዘው ምድር ባቡርን ሲቀላቀሉ አንድም ሴት የሌለ ሁሉም ወንዶች ብቻ የነበሩ ቢሆንም እሳቸው ግን አቅሜን አሳያለሁ እጅ አልሰጥም ሠርቼ ለውጥ አምጥቼ ሴቶች በተሰማሩበት የሙያ መስክ ሁሉ ውጤታማ መሆን እንደማይሳናቸው አሳያለሁ ብለው ሥራውን በልበ ሙሉነት የዛሬ 39 ዓመት ገደማ ጀመሩት።

ብቸኛዋ ሴት የማሽን ባለሙያ ሆነው በጀመሩበት ምድር ባቡር ላይም ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ብዙ ሥራዎችን ስለማከናወናቸው የሚያውቋቸው አብረዋቸው የሠሩ ሁሉ የሚመሰክሩላቸው ሐቅ ነው።



ወይዘሪት አማረች ቦጋስ

**ለ39 ዓመት ገደማ ሥራም አንድም ቀን ደከመኝ ሰለቸኝ ብዬ አላውቅም፡፡ እንደ ሳይንሱ ከሆነ እኔ በምሠራው ዓይነት ሙያ ውስጥ ሴቶች ከአራት ዓመት በላይ ባይቆዩ ተብሎ ነው የሚመከረው**

አማረች በምድር ባቡር ውስጥ ያሉ የብረታ ብረት ሥራዎችን በሙሉ ይሠራሉ፤ ባቡሩ ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀስ በፉርጎዎቹ መካከልም ይሁን በሐዲዱ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን ከሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን በሚገባ ይጠግናሉ፤ በዚህም የበቁ ፤የነቁ ባለሙያ ስለመሆናቸው ይናገራሉ።

"......እኔ ድርጅቴን በሙያዬ ለማገልገል ደክሞኝ አያውቅም፤ ሁሌም ሥራ ካለ መሥራት የማውቀውን ለሌሎች ማሳወቅ ከእነሱም የምወስዳቸውን ትምህርቶች በንቃት ማየትና በተግባር መቀየር የሥራ መርሔ ነው" ይላሉ።

በአንድ ወቅት እንደውም ለአየር ኃይል የዳቦ ቤት እቃን በመገጣጠም ባበረከትኩት አስተዋፅዖ ከእኔ አልፎ ድርጅቴን የሚያስመሰግን ሥራ ሠርቻለሁ የሚሉት አማረች ከዛም የኢትዮጵያ አየር መንገድ በየቦታው ያሉ ኪዮስኮቹ ጥገና ሲያስፈልግቸው በብቃት በመጠገናቸው በአየር መንገዱም እውቅናና ምስጋና እንደተቸራቸው ያብራራሉ።

".......ምድር ባቡር ልጅ ሆኜ የተቀላቀልኩት መሥሪያ ቤት ነው፤ የልጅነትና የወጣትነት ጊዜዬንም አሳልፌበታለሁ፤ ለእኔ ቤቴ ማለት ነው። በሥራዬም ብዙ መልካም ነገሮችን አበረክቻለሁ ብዬ አስባለሁ፤ ብዙ ወጣቶችም እውቀትን አግኝተዋል የሚል እምነት አለኝ። ለ39 ዓመት ገደማ ሥራም አንድም ቀን ደከመኝ ሰለቸኝ ብዬ አላውቅም። እንደ ሳይንሱ ከሆነ እኔ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# 39 ዓመታት በባቡር…

ከ6ኛ ገጽ የዞረ

በምሠራው ዓይነት ሙያ ውስጥ ሴቶች ከአራት ዓመት በላይ ባይቆዩ ተብሎ ነው የሚመከረው። እኔ ግን ይህንን ሁሉ ዓመት ሠርቻለሁ። በዚህም ደስተኛ ነኝ። አሁንም የሥራው ፍቅርና ፍላጎት አብሮኝ ነው” በማለት ስለሥራቸው ይናገራሉ።

በድሬዳዋ ምድር ባቡር ታሪክ የመጀመሪያዋም ብቸኛዋም የሴት ቴክኒሻን ይሁኑ እንጂ የልፋታቸውን ያህል ወይም የሚገባቸውን ያህል ጥቅምም፤ እውቅናም ስላለማግኘታቸው ይናጋራሉ። ለዚህ ዋናው ምክንያት ደግሞ የከፍተኛ አመራሩ ለሴቶች ያላቸው ማበረታቻ በጣም የወረደ መሆኑ እንደሆነም ግምታቸውን ይናገራሉ።

“………እኔ ሥራ በጀመርኩበት ወቅት እንኳን ድሬዳዋ ምድር ባቡር ቀርቶ ጅቡቲና ፈረንሳይ ሀገርም ሴት ቴክኒሻን አልተቀጠረም ነበር። ከእኔ በኋላም አንዲት ሴት የመጣች ቢሆንም በሥራው ላይ ብዙ መቀጠል ሳትፈልግ ለቃለች። ከዛ በኋላም የመጣች አለች ነገር ግን ያን ያህል አይቆዩም። ምክንያቱ ሥራው ከባድ ስለሆነ ነው” ይላሉ።

በአንድ ሥራ ላይ ከፍ ያለ ዓመታትን ለመቆየት ዋናው ነገር ሥራውን ከልብ መፈለግና መውደድ ነው። ከዛ ደግሞ ራስን ለጥቅም ተገዢ አለማድረግ ወሳኝነት አለው የሚሉት አማረች ሰው ፍቅር ሳይኖረው ሥራ ቢጀምር ውጤታማ አይሆንም። ዛሬ ላይ ደግሞ ወጣቶች ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ ፍቅር ስላላቸው ደመወዝ ይላሉ እነዚህ ነገሮች ደግሞ ብዙ ርቀት አይወስዱም በማለት ያብራራሉ ።

“……እኔ ሥራ የጀመርኩት በ 285 ብር ደመወዝ ነው፤ ዛሬ ላይ ይህ ብር ይከፈል ወይም ሰው በዝቅተኛ ገንዘብ ሥራ ይሥራ እያልኩ አይደለም። ይህንም ቢባል ኑሮው ድሮና ዘንድሮ የሚገናኝ ባለመሆኑ ችግር ነው። ነገር ግን ወጣቶች ሴቶችም ይሁኑ ወንዶች ለፍታ ላስተማረቻቸው ሀገራቸው ምን ላበርክት ብለው ማሰብ ሲገባቸው ሙያቸውን በገንዘብ መቀየር ብቻ ከሆነ ሕልማቸው ችግር ይፈጠራል። በመሆኑም እነሱም ሳይጎዱ ያስተማረቻቸውም ሀገር ከእነሱ ማግኘት ያለባትን ነገር ሳታጣ አጣጥሞ መሄድን ማወቅ ያስፈልጋል” በማለት ሃሳባቸውን ይሰጣሉ።

ምድር ባቡርን እሳቸው እንደ ሁለተኛ ቤታቸው የሚያዩት ቢሆንም ሲቀጠሩ ጀምሮ ያለው የአሠራር ሂደት ግን እሳቸውን ያገለለ እንደሆነ ይሰማቸዋል። እንደውም ‹‹የሚሠራ ሰው የሚፈለግ አይመስልም›› በማለት ይናገራሉ። እኔ የምሠራውን ሥራ ጥቅምና ጉዳቴን ተቋሙ ያውቃል ጓደኞቼ ደግሞ የሚመሰክሩት ሐቅ ነው። ነገር ግን መሥሪያ ቤቱ ለእኔ ሴት ሆኜ ከባዱን የሥራ ዘርፍ መርጬ እየሠራሁ ምንም ያደረገልኝ ነገር የለም።›› በማለት የሚናገሩት አማረች ‹‹አንዳንዶች ትላንት ገብተው ዛሬ ቤት ተሰጧቸው፤ ሌላም ሌላም ነገር ተደርጎላቸው ይታያል ይህ ግን ሞራል የሚነካ ነገር መሆኑ ቢታወቅልኝ እወዳለሁ›› ይላሉ።

“……በዚህ ዘመን ሴት ልጅ ከወንድ እኩል ከሠራች ወንዱ ሲሠራ የነበረውን አስበልጣ ሠርታ ከተገኘች የማትበረታታበት ምክንያት ምንድን ነው፤ መንግሥት ሴቶችን ማብቃት ማበረታታት እያለ የሚያወራው እኮ በየመሥሪያ ቤቱ ያሉ ጠንካራ ሴቶችን እያበረታቱ ወደፊት ማምጣት እንዲቻል ነው እንጂ እየሠራች፤ እየለፋች ያለችን ሴት ትኩረት መንፈግ አይመስለኝም “ በማለት ይናገራሉ።

አማረች ያለፉትን 39 ዓመታት በጥንካሬ በከፍተኛ ወኔና በደስታ ነው ሲሠሩ የኖሩት። ዛሬም በሥራው ላይ ናቸው። በእነዚህ ሁሉ ዓመታት ግን አንድም ቀን አሟቸው ወይም ደግሞ ሥራውን ልተወው በቃ ብለው አያውቁም። ለዚህ ብርታታቸውና ጥንካሬያቸው ዋናው ምክንያት የሰው ፍቅር ቢሆንም ጎን ለጎን ደግሞ በየቀኑ ከሥራ ወደቤት ከቤት ወደሥራ የሚያደርጉት የብስክሌት ጉዞም ስለመሆኑ ይናገራሉ።

ወንድ የሥራ ባልደረቦቻቸው እንደ ራሳቸው



እንደሚያዩዋቸው የሚናገሩት አማረች እነሱ የሚሠሩትን ሁሉ ስለምሠራ ይደክማታል፤ ቆይ ይሄ ለሴት አይሆንም ብለው ተጨንቀውም አያውቁም፤ እኔም እንደዛ እንዲሰማቸው ስለማልፈልግ የምሠራውን ሥራ በከፍተኛ ሞራልና ቁርጠኝነት ነው የማከናውነው በማለት ይናገራሉ።

አማረች ውጪ የሚውሉ በተለይም የወንድ ሥራ እየሠሩ ከወንዶች ጋር የሚውሉ ከመሆኑ አንጻር እንደው ማኅበራዊ ሕይወቱንስ እንዴት እየገፉት ነው ስላቸው እየሳቁ”…….ማኅበራዊ ኑሮ ላይ ተሳትፎ አደርጋለሁ፤ በቀበሌም ይሁን በሴቶች ማኅበር በኩል ያሉ ተሳትፎዎችን እሳተፋለሁ ነገር ግን እንደ ሴቶች ወጥ መሥራት አልያም ለመሥሪያ የሚሆን ግብዓቶችን ማዘጋጀት ላይ ሰነፍ ነኝ፤ የሚገርምሽ በሥራ ቦታ ላይ ሆነን በዓል ከሆነ እርድ ይፈጸማል በዚህ ሂደት ውስጥ የእኔ ሚና የሚሆነው ቁጭ ብዬ መከታተልና ምግቡ ተሠርቶ ሲጠናቀቅ መመገብ እንጂ በሥራው ላይ ተሳትፌ አላውቅም፤ እነሱም ስሪ አይሉኝም” በማለት ይናገራሉ።

“…….ሴት ልጅ ጥፍሯን ፀጉሯን አሳምራ ሥራ ብትሄድ ነው የምትመርጠው የኅብረተሰቡም አመለካከት ይኸው ነው፤ እኔ ግን እንደ ወንዶች ቱታ ለብሼ፤ እጄም ግሪስ ነክቶ መሬት ላይ ተንደባልዬ ነው ሥራዬን በአግባቡ የምወጣው እንደእኔ አይነት ሴት ቴክኒሻንም አለ ብዬ ለማለት ይከብደኛል፤ እኔ ግን በሥራዬ በጣም ደስተኛ ነኝ አቅሜ እስከፈቀደም ድረስ እሠራለሁ” ይላሉ።

ድሮ በእኛ ጊዜ ሴት እንኳን እንደ እኔ አይነት ሥራ ቀርቶ ሌሎቹንም ሥራዎች ልሥራ ስትል ብዙ

**"………እኔ ሥራ በጀመርኩበት ወቅት እንኳን ድሬዳዋ ምድር ባቡር ቀርቶ ጅቡቲና ፈረንሳይ ሀገርም ሴት ቴክኒሻን አልተቀጠረም ነበር**

የሚገጥሟት መሰናክሎች ነበሩ፤ ዛሬ ላይ መጠነኛ መሻሻሎች ይታያሉ። ሴቶች የወንዶች የሚባሉ ሥራዎችን እየሠሩ ነው። በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ አውቶቡስ ላይ የማያቸው ሴት አሽከርካሪዎች በጣም ደስ ይሉኛል፤ ያኮሩኛልም በማለት ሴቶች እየተሳተፉባቸው ስላሉ የሥራ መስኮች ይናገራሉ።

አማረች የሚወዷቸው አባታቸው ሕመምና ሞት ብዙ እንደጎዳቸው ይናገራሉ፤ በተለይም አባታቸው ካረፉ በኋላ እናታቸውን የመንከባከብ አብሮ የመሆን ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ እሳቸው ላይ መውደቁ በትምህርታቸው እንዳይገፉ በተለይም ደግሞ ከሀገር ውጪ ሄዶ የመኖር የመለወጥ ሕልማቸውን እውን እንዳያደርጉት እንዳደረጋቸውም ነው የሚናገሩት።

ሌላው አማረች የባቡር አሽከርካሪ ለመሆን ፍቃደኝነቱም ፍላጎቱም ነበራቸው፤ ነገር ግን እስከ አሁን በሙያው ያልገቡት እሳቸው የሚፈልጉት ሰዎችን አሳፍሮ የሚሄደውን ባቡር ማሽከርከር ነው፤ ድርጅቱ ደግሞ አሽከርካሪ ከሆኑ የሰውንም የእቃም ማጓጓዣ ባቡርን ማሽከርከር ግዴታ ነው ማለቱ ወደሙያው እንዳይገቡ እንዳራቃቸውም ይናገራሉ።

“…….ባቡር እንዳሽከረክር አዲስ አበባ ያሉ ሴት ሠራተኞች ሳይቀሩ ሀሳብ አቅርበዋል፤ እንዲሁም ብዙ ድጋፎችና ማበረታቻዎችን ሲያደርጉልኝ ነበር። ነገር ግን ድርጅቱ የእቃና የሰው ማጓጓዣ ባቡሮች ያሉት በመሆኑ ባቡር መንዳት ከፈለኩ ሁለቱም ላይ ተሳታፊ መሆን አለብሽ ብሎኛል። የእቃ ማጓጓዣ ባቡሮች ደግሞ ሁለትና ሦስት ቀን መንገድ ላይ ይቆያሉ (ያድራሉ) ለእኔ ደግሞ ያ ነገር ብዙም አይመቸኝም፤ ከዚህ አንጻር የሰው ማጓጓዣው ላይ ብቻ ልሥራ ብልም ተቀባይነት ባለማግኘቴ እስከ አሁን ባቡር አላሽከረከርኩም” በማለት የባቡር አሽከርካሪ ያልሆኑበትን ምክንያት ያስረዳሉ።

ምንም እንኳን አማረች በድርጅቱ ውስጥ ከ39 ዓመት ያላነሰ የአገልግሎት ጊዜ ቢኖራቸውም ተቋሙ ግን በደንብ ይዟቸዋል ለማለት የሚያስደፈር አይደለም። ለዚህ ማሳያው ደግሞ ለሌሎች ባለሙያዎች በጅቡቲና በሌሎች አገሮች የሚደረገው የልምድ ልውውጥ ሥልጠናና ሌሎች ነገሮች እሳቸው ጋር ደርሰው አያውቁም። በዚህ ቅር ቢላቸውም መሥሪያ ቤታቸውን ግን ወደውት እስከ አሁን እየሠሩ ነው።

“……..እውነት ለመናገር ምድር ባቡር ያሉ አመራሮች ተፅዕኗቸው ከባድ ነው እንጂ በተቋሙ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያዋ የሴት ቴክኒሽያን ሆኜ ጅቡቲን እስከ አሁን አላየኋትም፤ ምክንያቱም አለቆቻችን ጥሩ አመለካከት የላቸውም፤ እስከ አሁን በሥራዬም አገኘሁት የምለው ነገር ድርጅቱን በቅንነት ማገልገሌን እኔ ለወንዶቹ ጓደኞቼም ብርታት መሆኔን እንጂ በጥቅም ደረጃ ከደመወዜ በቀር የማውቀው ምንም ሽልማትም ሆነ ስጦታ የለም” በማለት ሁኔታውን በኃዘን ይገልጹታል።

አማረች እስከ አሁን ድረስ ትዳር ይዘው ቤተሰብ ለመመሥረት አልቻሉም ለዚህ ደግሞ “……ብዙ ጊዜ ከወንዶች ጋር መዋሌ ፤ ሥራዬም የወንድ መሆኑ አብዛኛውም ሰው ከወንድ እንጂ ከሴት እኔን መመደብ አለመቻሉ ምናልባት ተፅዕኖ አሳድሮብኝ ይሆናል የሚል ግምት አለኝ፤ ግን ደግሞ እኔም በዛ ውስጥ እያለፍኩ ስመጣ ለሁኔታው ፍላጎት እያጣሁ መጣሁና ትዳርም ቤተሰብም ለመመሥረት የነበረኝ ጉጉት በዛው ቀረ” በማለት ይናገራሉ።

አሁን ላይ ምድር ባቡር ውስጥ የተለመደ ሥራቸውን እያከናወኑ የሚገኙት ብርቱዋና ጠንካራዋ አማረች ዛሬ ላይ ድርጅቱ ውስጥ የሠራተኞችን ኅብረት እንደሚመሩ በሙሉ ድምፅ ተመርጠው ከሥራቸው ጎን ለጎን በማገልገል ላይ ናቸው።

አማረች ወደፊት ቢሆንልኝ ብለው የሚመኙት ይህንን ነው፤”……ሰዎች ተበድለው በደላቸውን የሚከስ ፍትሕ አጥተው ሳይ በጣም አዝናለሁ፤ እኔም ቢሆንልኝና ቢሳካልኝ የእነዚህን ሰዎች እንባ የማብስበት አቅም ቢኖረኝ ብዬ እመኛለሁ፤ ከፈጣሪ ጋርም ወደፊት የምሠራው ይመስለኛል “።

# ዓለም አቀፍ መድረኮች - ለቱሪዝም ዘርፉ እድገት

ዳግም ከበደ




ሀገሮች ቱሪዝምን መሠረት ያደረጉ በርካታ ዓለም አቀፍ የንግድ ዓውደ-ርዕይና ትርዒቶችን ያዘጋጃሉ። የቱሪዝም መስህብ ያላቸው ሀገራትም ጎብኚዎችን ለመሳብና ገፅታ ለመገንባት በእነዚህ ዓለም አቀፍ መሰናዶዎች ላይ ይሳተፋሉ። ባሕላዊ፣ ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊና መሰል እሴቶቻቸውን (የቱሪዝም መዳረሻዎቻቸውን) የሚገልፁ ማስታወቂያዎችና ዝግጅቶችን በማሰናዳትም ተደራሽነታቸውን ለማስፋት ይጥራሉ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ዓለም አቀፍ የቱሪዝም የንግድ ትርዒቶችና ዓውደ-ርዕይ ዝግጅቶች ተቀባይነታቸው እየጨመረ መጥቷል። ቱሪስቶች የጉብኝት እቅድ ለማውጣትና በቂ መረጃ ለማግኘት በእነዚህ መሰናዶዎች ላይ ትኩረታቸውን ያደርጋሉ። ሀገራቱም አስጎብኚዎች፣ የቱሪዝም ተቋማትን እና መሰል ባለድርሻዎችን በትርዒቶቹ ላይ በማሳተፍ አስፈላጊ የሚሏቸውን መረጃዎች ተደራሽ ያደርጋሉ። ይህ ጥረት ለዓለም አቀፍ የቱሪዝም ዘርፍ እድገት ጉልህ አስተዋፅዖ እያበረከተ መሆኑን በጉዳዩ ላይ ጥናት ያደረጉ ተቋማት ይገልፃሉ።

በዓለማችን በቱሪዝም ትርዒትና ዓውደ-ርዕይ ከሚታወቁ ቀዳሚ ዝግጅቶች መካከል በየዓመቱ መጋቢት ወር ላይ ለተከታታይ አምስት ቀናት የሚካሄደው አይ.ቲ.ቢ በርሊን /የዓለም ትልቁ የቱሪዝም ኤክስፓ/ ተጠቃሽ ነው። ይህ ዓለም አቀፍ ዓውደ-ርዕይ እ.ኤ.አ በ1966 ስያሜውን ይዞ ከአምስት ሀገራት በተውጣጡ ዘጠኝ ተሳታፊዎች የተጀመረ ነው። እስከ እ.ኤ.አ 2019 ድረስ በተመዘገበው መረጃ መሠረትም በየዓመቱ በመሰናዶው ላይ ሁለት መቶ ሺ የሚደርሱ ጎብኚዎች ይገኛሉ።

ኢትዮጵያም የቱሪዝም ሀብቶቿን ለማስተዋወቅ በዚህ ዝግጅት ላይ በአስጎብኚ ድርጅቶች፣ በኢትዮጵያ አየር መንገድ እንዲሁም በቱሪዝም ሚኒስትር በመወከል ትሳተፋለች። ዘንድሮም በበርሊን ጀርመን የተካሄደው ዓለም አቀፍ የቱሪዝም ኤግዚቢሽን (ITB) በይፋ ሲከፈት ኢትዮጵያ መሳተፏን የቱሪዝም ሚኒስቴር አስታውቋል። ይህ ኤግዚቢሽን በመላው ዓለም የሚገኙ ስመጥር የቱሪዝም ኩባንያዎችና ሀገራት የቱሪዝም አገልግሎታቸውን የሚያስተዋውቁበት መድረክ እንደመሆኑ ኢትዮጵያም የዚህ እድል ተጠቃሚ ለመሆን ተሳታፊ መሆኗን አስታውቋል።

በዓውደ-ርዕዩ ላይ የቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ ተገኝተው ኢትዮጵያ በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለዘርፉ ትኩረት በመስጠት እያከናወነች ያለችውን የመዳረሻ ልማትና የቱሪስት መስሕቦችን አስተዋውቀዋል። ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋርም ለመሥራት የሚያስችላቸውን ውይይት ማድረጋቸውን የሚኒስቴሩ የህዝብ ግንኙነት ክፍል ስራ አስፈጻሚ አቶ አለማየሁ ጌታቸው ለዝግጅት ክፍላችን መረጃ አስታውቀዋል።

በዘንድሮው የበርሊኑ አይ.ቲ.ቢ ዓውደርዕይ ላይ የኢትዮጵያ አየር መንገድን ጨምሮ በርካታ የሀገር ውስጥ የቱሪዝም አገልግሎት ሰጪዎች ተሳትፈዋል፤ ኢትዮጵያ አይ.ቲ.ቢን ጨምሮ የቱሪዝም መስሕቦችን ለማስተዋወቅ በተለያዩ ጊዜያት በበርካታ ታዋቂ ዓለም አቀፍ ዓውደ ርዕዮች ላይ ተሳትፋለች።

እውቅ ዝግጅቶች በቱሪዝም ኢንዱስትሪው ተመራጭ ከመሆናቸውም በላይ በርካታ ቱሪስቶችን ለማግኘትና መስሕቦችን ለማስተዋወቅ ሁነኛ አቅሞች ናቸው። በእነዚህ ታዋቂ ዓውደ-ርዕዮች ውስጥ የቫንኮቨር ዓለም አቀፍ የጉዞ ኤክስፖ፣ የኒዮርክ ታይምስ የጉዞ ትርዒት፣ የላስ ቬጋስ የጉዞ ወኪሎች ፎረምና የዓለም የጉዞ ገበያ በለንደን ይገኙበታል።

አቶ ጌትነት ይግዛው በቱሪዝም ሚኒስቴር ኮንቬንሽን ቢሮ መሪ ሥራ አስፈፃሚ ናቸው። ኢትዮጵያ ቀደም ባሉት ጊዜያት የቱሪዝም መስሕቦቿን በዓለም አቀፍ አውደ ርዕዮች ላይ ስታስተዋውቅ ሀገሪቷን በመወከል ይታወቃሉ። በርከት ባሉ መሰል ዝግጅቶች ላይ ይሳተፋሉ።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ ዓለም አቀፍ የቱሪዝም ኤክስፖዎችንና የንግድ ዓውደ-ርዕዮችን ልክ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚካሄዱት ባሕላዊ ገበያዎች ይመስሏቸዋል። ነጋዴዎች ምርቶቻቸውን ለመሸጥ እነዚህን ባሕላዊ ገበያዎች እንደሚጠቀሙት ሁሉ ኢትዮጵያም በታዋቂ የንግድ ትርዒቶች፣ ኤክስፖዎችና ዓውደ ርዕዮች ላይ ተሳታፊ በመሆን የቱሪዝም ሀብቶችን፣ ባሕላዊ እሴቶችን፣ ታሪካዊ ቦታዎችንና መሰል የዘርፉ ሃብቶችን ለማስተዋወቅ እንዲሁም ጎብኚዎችን በመሳብ ጥቅሎችን ለመሸጥ እንድትችል ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው፡፡

በእነዚህ ዓውደ-ርዕዮች ላይ የገበያ ስልቶችን ተጠቅሞ የኢትዮጵን የቱሪዝም ሀብቶች ለማስተዋወቅና የቱሪዝም ምርቶችን ለመሸጥ እድል የሚከፍት ነው የሚሉት መሪ ሥራ አስፈፃሚው፤ አራት አይነት የገበያ አይነት ወይም መንገዶች መኖራቸውን ይናገራሉ። የመጀመሪያው ኢትዮጵያ ያሏትን ባሕላዊ እሴቶችና ምርቶች፣ ታሪካዊ ስፍራዎችና የመስሕብ መዳረሻዎችን የሚወክሉ ምርቶችን ጥራት ባለው መንገድ በዓውደ-ርዕዮቹ ላይ ማቅረብ እንደሆነ ይገልፃሉ።

አቶ ጌትነት እንደሚናገሩት፤ ከገበያ ስልቶቹ በኢንተርናሽናል የቱሪዝም ኤክስፖና ዓውደ-ርዕዮች ላይ ተግባራዊ የሚደረገው ሁለተኛው ተግባር ማስተዋወቅ ነው፡፡ ለኢትዮጵያም አዳዲስ የቱሪዝም መዳረሻዎች፣ ባሕላዊ እሴቶች፣ የቱሪዝም አገልግሎት ዘርፍ አገልግሎቶችን፣ ሌሎች የዓለም ሀገራትና ጎብኚዎች የማያውቋቸውን የቱሪዝም መስሕቦች ለማስተዋወቅ በር ይከፍታል፡፡

ሌላው በገበያ ስልት ውስጥ የሚጠቀሰው ቦታ መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህም የኢትዮጵያን የቱሪዝም ሀብቶች አስተዋውቆ ቱሪስቶችን በብዛት ለማግኘት የሚቻልበትን ትክክለኛ ስፍራ መለየት እንደሆነ ይናገራሉ። ከዚህ ሳይንሳዊ ስልት አንፃር በዓለም በጉብኝት ባሕላቸው የሚታወቁት ምዕራባውያን፣ በኤሺያና ሌሎች አሕጉራት በሚካሄዱ ዓለም አቀፍ የቱሪዝም ዓውደ-ርዕዮች የኢትዮጵያን እሴቶችና የመስሕብ ሀብቶች ማስተዋወቅ ትክክለኛው አማራጭ መሆኑን ይጠቅሳሉ።

በዚህ መሠረት ኢትዮጵያም ሀብቶቹን በጥራት ማስተዋወቅ በሚቻልባቸው ኤክስፖ፣ ዓውደ-ርዕይና ትርዒቶች ላይ በተደጋጋሚ መቅረብ እንደሚጠበቅባት ያስረዳሉ። የኢትዮጵያን የመስሕብ ስፍራዎች የሚጎበኙ ሁሉ አገልግሎቱን በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ ለማድረግና ለማስተዋወቅ መድረኮቹ ጠቃሚ ስፍራዎች መሆናቸውን አቶ ጌትነት ይገልፃሉ።

በዓለም አቀፍ ዓውደ ርዕዮች ላይ በሆቴል ዘርፍ የሆቴል ባለቤቶች እንዲሁም በአስጎብኚ ድርጅቶች (tour operators) አማካኝነት ኢትዮጵያ መወከል ይገባታል የሚሉት አቶ ጌትነት፤ እንደየቱሪስቱ ፍላጎትና ባሕሪ የተፈጥሮ ቱሪዝም፣ የባሕል ቱሪዝም፣ በታሪክና ቅርስ ላይ መሠረት ያደረጉ ጥቅሎችን አዘጋጅተው ጎብኚዎች ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ የማስተዋወቅ ሥራ መተግበር እንደሚገባቸው ይናገራሉ። ይህን መሰል ተግባር ለማከናወን ደግሞ እንደ አይቲቢ በርሊን ያሉ ታዋቂ ዓለም አቀፍ መድረኮች ተመራጭ መሆናቸውን ያስረዳሉ።

«ከአስር ዓመት በፊት ኢትዮጵያ 12 በሚደርሱ ዓለም አቀፍ የገበያ መድረኮች ላይ ተሳትፋ ነበር» የሚሉት መሪ ሥራ አስፈፃሚው፤ አሁን ግን ቁጥሩ በጣም ዝቅ ብሎ አይ.ቲ.ቢ በርሊንና የዓለም የጉዞ ገበያ በለንደን ላይ ብቻ እየተሳተፈች እንደሆነ ይናገራሉ። ኢትዮጵያ መሰል ዓለም አቀፍ መድረኮችን መሳተፍ የጀመረችው የቱሪዝም አባት ተብለው በሚታወቁት አቶ ሀብተሥላሴ ታፈሰ አማካኝነት ከ1970ዎቹ ጀምሮ እንደነበርም ይገልፃሉ። ይህ ልምድ እየቀነሰ መምጣቱ ተገቢ አለመሆኑን አስገንዝበው፤ ዳግም ሊነቃቃ እንደሚገባ ይመክራሉ።

> **በታላላቅ ዓውደ-ርዕዮች ላይ የኢትዮጵያን የቱሪዝም መስሕቦች ለማስተዋወቅ በትክክለኛው ቦታ ተገቢ ባለሙያ መጠቀምም አስፈላጊ ነው። ይህ ሲሆን ኢትዮጵያ ያላትን እምቅ ሀብት በፍፁም ሙያዊ ሥነ-ምግባርና በጥልቅ እውቀትና መረጃ ታግዞ ለቱሪስቶች ማስተዋወቅና ውጤት ማምጣት ይቻላል**

መሪ ሥራ አስፈፃሚው እንደሚያብራሩት፤ በታላላቅ ዓውደ-ርዕዮች ላይ የኢትዮጵያን የቱሪዝም መስሕቦች ለማስተዋወቅ በትክክለኛው ቦታ ተገቢ ባለሙያ መጠቀምም አስፈላጊ ነው። ይህ ሲሆን ኢትዮጵያ ያላትን እምቅ ሀብት በፍፁም ሙያዊ ሥነ-ምግባርና በጥልቅ እውቀትና መረጃ ታግዞ ለቱሪስቶች ማስተዋወቅና ውጤት ማምጣት ይቻላል። የተቋም ግንባታ አስፈላጊ ቢሆንም ትክክለኛና ተገቢ ባለሙያዎችን ማሳተፍ የማይቻል ከሆነ በመሰል መድረኮች ላይ መሳተፍ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል፡፡

አቶ ጌትነት ከ12 ዓለም አቀፍ የማስተዋወቅ መድረኮች ወደ ሁለት የተወረደበት ምክንያት በተለያየ ጊዜ የሚፈጠረው የአደረጃጀት ለውጥ ተፅዕኖ መሆኑን ይገልፃሉ። መድረኮቹ ላይ በመሪነት ይሳተፍ የነበረው መዋቅር አንድ ጊዜ በባሕልና ቱሪዝም ሌላ ጊዜ ደግሞ በቱሪዝም ድርጅትና በቱሪዝም ኢትዮጵያ በሚሉ ስያሜዎች በየጊዜው የመዋቅር ለውጥ እያመጣ መደራጀቱና አለመረጋጋቱ በቋሚነት፣ በጥራትና በብዛት የንግድ ትርዒቶቹ ላይ ኢትዮጵያ ተሳታፊ እንዳትሆን እንቅፋት መፍጠሩን ያስረዳሉ።

መንግሥት በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ የኢትዮጵያን የቱሪዝም ሀብቶች ለማስተዋወቅና የቱሪስት ፍሰቱን ለማሳደግ የግል ዘርፉን በባለቤትነት ሊያሳትፍ እንደሚገባ የሚናገሩት መሪ ሥራ አስፈፃሚው፤ ይህን ማድረግ ካልተቻለ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት አዳጋች መሆኑን ነው ያስረዱት።

በኢትዮጵያ ውስጥ ከ500 በላይ አስጎብኚ ድርጅቶች፣ ከ700 በላይ ሆቴሎች እንዲሁም በርካታ የቱሪዝም ምርት አቅራቢ ባለቤቶች መኖራቸውን ገልፀው፤ እነዚህ ባለድርሻዎች የበኩላቸውን ተፅዕኖ ማሳረፍ የሚችሉበት አደረጃጀት መፍጠር እንደሚጠበቅበት ይናገራሉ። በተለይ በኮቪድ ወረርሽኝና በልዩ ልዩ ሰው ሠራሽ ግጭቶች የተዳከሙትን የግሉ ዘርፍ አንቀሳቃሾች መደገፍና ማነቃቃት አንደሚያስፈልግ ያሳስባሉ። ይህ ሲሆን የኢትዮጵያን ሀብት ማስተዋወቅና የቱረስት ፍሰቱን ከጊዜ ወደ ጊዜ በማሳደግ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ይገልፃሉ።

የኮንቬንሽን ቢሮው መሪ ሥራ አስፈፃሚው አቶ ጌትነት በበርካታ ዓለም አቀፍ የቱሪዝም የጉዞ ዓውደ ርዕዮች ላይ ከመሳተፍ ባሻገር መሰል ዝግጅቶችንም በኢትዮጵያ ውስጥ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ያመለክታሉ። ይህ ዝግጅት ዓለም አቀፍ ደረጃውን ከጠበቀና ሌሎች ሀገራትንም ያሳተፈ ከሆነ በቀላሉ የመስሕብ ሀብቶችን በዚሁ በኢትዮጵያ ማስተዋወቅና ጎብኚዎችን በብዛት መሳብ እንደሚቻል ያስረዳሉ። ሆኖም በቅድሚያ ትላልቅ የኮንቬንሽን ማዕከላትን መገንባት ያሉትንም ደረጃቸውን ማሳደግ ተገቢ መሆኑን ያነሳሉ።

አዲስ አበባ 200 በላይ ዲፕሎማት ያላት እንዲሁም የአፍሪካ መዲና እንደሆነች የሚያነሱት መሪ ሥራ አስፈፃሚው፤ ይሁንና ግዙፍ መድረኮችን ለማዘጋጀት የሚያስችል ደረጃውን የጠበቀ የኮንቬንሽን ማዕከል እስካሁን በሚፈለገው ልክ መገንባት አለመቻሏን ያስረዳሉ። ይህንን ተግዳሮት መፍታትና ልክ እንደ አይ. ቲ.ቢ በርሊን እንዲሁም ሌሎች ታላላቅ የቱሪዝም የንግድ ትርኢቶችን በቋሚነት ማዘጋጀት እንደሚያስፈልግ ይገልፃሉ። ይህን ማድረግ ሲቻል የኢትዮጵያን የቱሪዝም ሀብቶች በሀገር ውስጥም ሆነ በውጪ ሀገራት በሚፈለገው ልክ ማስተዋወቅ እንደሚቻል ያስገነዝባሉ።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## ጀግናው ዑመር ሰመተር

**ዋስልኝ አየለ**

«ከአገሬ አፈር የሚደባልቅ ቤልጅግ እና ጎራዴ ይገፔ እንጂ ጫት ተሸክሜ የምመጣ እንዳይመስልህ!» በሚለው ንግግራቸው በብዙዎች ዘንድ ይታወቃሉ፤ ጀግናው ዑመር ሰመተር! የዚህ ሳምንት ክስተት ናቸውና ታሪካቸውን እናስታውሳለን።

**ከዚያ በፊት ግን በዚህ ሳምንት ብዙ ሴሎች ክስተቶች አሉና በአጭር በአጭሩ እናስታውሳቸው።**

ከ135 ዓመታት በፊት መጋቢት 1 ቀን የተጀመረውን የመተማ ጦርነት ባለው ሳምንት በዝርዝር አይተናል። በዕለቱ በጥይት የተመቱት አጼ ዮሐንስ 4ኛ ሕይወታቸው ያለፈው በዚህ ሳምንት መጋቢት 2 ቀን 1881 ዓ.ም ነበር። ደርቡሾችም እየተከታተሉ የአጼ ዮሐንስ አራተኛን አስከሬን ይዘው፤ አትባራ ወንዝ ላይ የነበሩ የኢትዮጵያ ወታደሮች ላይ ጥቃት አድርሰው፣ መጋቢት 3 ቀን 1881 ዓ.ም የአጼ ዮሐንስ አራተኛን ጭንቅላት ወሰዱ።

ከ4 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መጋቢት 4 ቀን 2012 ዓ.ም ዓለምን አስጨንቆ የነበረው ኮቪድ-19 ኢትዮጵያ ውስጥ መገኘቱ ይፋ ሆነ። በእያንዳንዱ ሰው የሕይወት ታሪክ ውስጥ አስጨናቂ ትዝታ ያለው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ እነሆ የታሪክ አካል ሆኖ አጋጣሚዎቹ ሲታወሱ ይኖራሉ።

ከ112 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መጋቢት 5 ቀን 1904 ዓ.ም የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ አባት የሆኑት ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ ተወለዱ። አክሊሉ ሀብተወልድ ኢትዮጵያን ወክለው ከኃያላን አገራት ጋር ተከራክረዋል፣ በተለያዩ ጊዜያት የኢትዮጵያን ጥቅም አስከብረዋል። በዚህ ጥረታቸው በዲፕሎማሲ ታሪክ ውስጥ በአርዓያነት ይጠቀሳሉ።

ከ61 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መጋቢት 5 ቀን 1955 ዓ.ም ባለፈው ጥር ወር በአፀደ ሥጋ የተለየን እና «ተንቀሳቃሹ ቤተ መጻሕፍት» በሚል ቅጽል ስም የታወቀው ገነነ መኩሪያ ተወለደ።

ከ148 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መጋቢት 7 ቀን 1868 ዓ.ም ኢትዮጵያ ከግብፅ ጋር ካደረገቻቸው ጦርነቶች መካከል አንዱ የሆነውና በኢትዮጵያ አሸናፊነት የተጠናቀቀው የጉራዕ ጦርነት ተካሄደ።

ከ96 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መጋቢት 7 ቀን 1920 ዓ.ም ካርል ሄይንዝ በም («የሰዎች ለሰዎች» በጎ አድራጎት ድርጅት መሥራች) ተወለዱ። ሰዎች ለሰዎች (ሜሽን ፎር ሜሽን) ድርጅት በኢትዮጵያ ውስጥ ትምህርት ቤቶችን፣ ሆስፒታሎችን እና ሌሎች የመሠረተ ልማት ሥራዎችንና የበጎ አድራጎት ሥራዎችን በመሥራት ይታወቃል።

**አሁን ወደ ጀግናው ዑመር ሰመተር ታሪክ እንለፍ።**

«ከአገሬ አፈር የሚደባልቅ ቤልጅግ እና ጎራዴ ይገፔ እንጂ ጫት ተሸክሜ የምመጣ እንዳይመስልህ!» የሚለው ንግግራቸው በቃል ጭምር ይነገርላቸዋል። ፋሽስቱን ጣሊያን መግቢያ መውጫ ካሳጡ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ጀግኖች አንዱ የሆኑት የምሥራቁ አርበኛ ደጃዝማች ዑመር ሰመተር፤ ከ80 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መጋቢት 6 ቀን 1936 ዓ.ም ሕይወታቸው ያለፈ የዚህ ሳምንት ክስተት ናቸው።

በፋሺስት ኢጣሊያ ወረራ ወቅት ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት የተጋደሉትና ደማቅ የጀግንነት ታሪክ የፃፉት ጀግናው አርበኛና ግዛት አስተዳዳሪ ደጃዝማች ዑመር ሰመተር በ1871 ዓ.ም በኦጋዴን አካባቢ ካልካዩ በተባለ ሥፍራ ተወለዱ። ለአካለ መጠን ከደረሱም በኋላ የኤልቡር አካባቢ ገዢ በመሆን አገልግለዋል። ኢጣሊያ ዓድዋ ላይ የደረሰባትን ሽንፈት ለመበቀል የያዘችውን የረጅም ጊዜ ዓላማ ለማሳካት ባደረገችው ወረራ ወቅት በምሥራቁ የኢትዮጵያ ክፍል ከደጃዝማች አፈወርቅ ወልደሰማያት ጋር ተሰለፉ። ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ለመውረር የጫረችው የወልወል ጠብ የተከሰተው ደግሞ ዑመር ሰመተር በነበሩበት በምሥራቁ የኢትዮጵያ ክፍል ነበር።

ኢጣሊያ በ1888 ዓ.ም ዓድዋ ላይ የደረሰባትን ሽንፈት ለመበቀልና ኢትዮጵያን የኢጣሊያ ምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛት አካል ለማድረግ ለ40 ዓመታት ያህል ስትዘጋጅና ጊዜ ስትጠብቅ ቆየች። እንደ አውሮፓውያኑ የዘመን ቀመር በ1922 ወደ ሥልጣን የመጣው ቤኒቶ ሙሶሊኒ፣ ኢጣሊያ ዓድዋ ላይ የተከናነበችውን የውርደት ማቅ እንደሚበቀልና ኢትዮጵያ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት አካል እንደምትሆን መዛት የጀመረው ገና በጠዋቱ ነበር።

ለዚህም እንዲያመቸው የኢጣሊያ መንግሥት ራስ ተፈሪ መኮንን ኢጣሊያን በጎበኙበት ወቅት «ቪቫ ኢትዮጵያ» እያለ ወዳጅ መስሎ ሸነገላቸው። እስከ አፍንጫው የታጠቀ በርካታ ጦር በኤርትራና በሌሎች የኢጣሊያ ምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛት አካባቢዎች ላይ ያከማች ጀመር። የጦሩን ውጤታማነት አስተማማኝ ለማድረግም ሐኪሞችን፣ ሰላዮችንና ሌሎች ሙያተኞችን አብሮ አጓጓዘ። ኢትዮጵያውያን የግዛት ባላባቶችን በጥቅም በመደለል ማስኮብለሉንና መረጃ መመንተፉንም ተያያዘው። በጨካኝነታቸው የታወቁትን እነ ኢሚሊዮ ዴ ቦኖ፣ ፒየትሮ ባዶሊዮ፣ ሩዶልፎ ግራዚያኒና ሌሎች የጦር አለቆችን ወደ ምሥራቅ አፍሪካ ላከ።

ጣሊያን ይህንን ዝግጅት ካጠናቀቀች በኋላም ኢትዮጵያን የምትወርበት አጋጣሚ መጠባበቅ ጀመረች። በዕለተ ረቡዕ፣ ኅዳር 26 ቀን 1927 ዓ.ም የኢጣሊያ ወታደሮች በኢትዮጵያ እና በእንግሊዝ ሱማሌላንድ (British Somaliland) መካከል ያለውን ወሰን ለመከለል የተላኩትን ሰዎች ይጠብቁ በነበሩት የኢትዮጵያ ወታደሮች ላይ ጥቃት ከፈቱባቸው። (ኢጣሊያ በአካባቢው ያለው የኢጣሊያ ሱማሌላንድ ግዛቷ ስለሆነ ወታደሮቿ በአካባቢው ነበሩ)

ውጊያ ተደረገና በሁለቱም ወገኖች በኩል ሰውነት ቆሰለ፤ አካል ጎደለ ... የሰው ሕይወት ጠፋ።

ኢትዮጵያም ስሞታዋን ለኢጣሊያ መንግሥት ስታቀርብ፤ የኢጣሊያ መንግሥት ይባስ ብሎ የተበደለ መሆኑን በመግለፅ የሚከተሉትን «የመደራደሪያ ጥያቄዎች» አቀረበ።

አንደኛ፤ የወቅቱ የሐረርጌ ገዢ የነበሩት ደጃዝማች ገብረማርያም ወልወል ድረስ ሄደው እዚያ የሚገኘውን የኢጣሊያ የጦር መሪ በኢትዮጵያ መንግሥት ስም ይቅርታ እንዲጠይቁ፣ አንድ የኢትዮጵያ የጦር ጓድ ለኢጣሊያ ሰንደቅ ዓላማ ሰላምታ እንዲሰጥ፣ በኢትዮጵያ በኩል ለተደረገው የማጥቃት እርምጃ ኃላፊ የሆኑት ባለሥልጣኖች ሁሉ ተይዘው የኢጣሊያን ሰንደቅ ዓላማ እጅ ነስተው እንዲሻሩና ተገቢውን ቅጣት በአስቸኳይ እንዲያገኙ፣

ሁለተኛ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ለቆሰሉት፣ አካላቸው ለጎደለውና ለሞቱት የኢጣሊያ ወታደሮች ካሣ የሚሆን 200 ሺህ ማርቴሬዛ (ጠገራ ብር) እንዲከፍል እንዲሁም

3ኛ፤ በኢጣሊያ ወታደሮች ላይ ጥቃት ፈፅመው ከባድ ጥፋት ያደረሱት ዑመር ሰመተር ተይዘው ለኢጣሊያ መንግሥት እንዲሰጡ ... በማለት የለየለት የትዕቢት ጥያቄ አቀረበ።

የኢትዮጵያ መንግሥትም የኢጣሊያን ሃሳብ ሳይቀበል ቀረ፤ ጉዳዩ በእርቅ እንዲያልቅ ለማድረግ ቢጥርም ሳይሳካ ቀረ። ከዚህ በኋላ ፋሺስት ኢጣሊያ ለ40 ዓመታት ያህል ስትዘጋጅበት የቆየችውን እቅድ እውን ለማድረግ በሁሉም አቅጣጫዎች ኢትዮጵያን መውረር ጀመረች።

በዓለም አቀፍ ሕግጋት ፈፅሞ የተከለከሉ የጦር መሣሪያዎችን (የጦር አውሮፕላን፣ የመርዝ ጋዝ፣ ...) ጭምር በመጠቀም በኢትዮጵያውያን ላይ እጅግ በጣም ከባድ የሆነ የጦር ወንጀል ፈፀመች።

ኢጣሊያ የኢትዮጵያን ግዛት እወስዳለሁ ብላ ወልወል ላይ የጫረችው እሳት በሁለቱም ወገኖች ላይ ጉዳት አድርሶ ነበር። በኋላም እርቀ ሰላም አወርዳለሁ ብላ ቃል ስትገባም ድርድር ስታቀርብ የግጦሽ መሬት ከኢትዮጵያ ግዛት ተቆርሶ እንዲሰጣት ስትጠይቅ «በኢጣሊያ ወታደሮች ላይ በደል የፈፀመው ዑመር ሰመተር እጁ ተይዞ ተላልፎ ይሰጠኝ» ብላ ጠይቃ ነበር። ዑመር ሰመተርም ይህን ሲሰሙ «ከሀገሬ አፈር የሚደባልቅ ቤልጅግና ጎራዴ ይገፔ እንጂ ጫት ተሸክሜ የምመጣ እንዳይመስልህ» ብለው በመመለስ ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ከመውረር እንድትታቀብ ደጋግመው ያስጠነቅቁ ነበር።

በወልወል የተጫረው እሳት በሰሜንም ቀጠለ፤ በመላው ሀገርም ተዳረሰ። ዑመር ሰመተር ከደጃዝማች አፈወርቅ ወልደሰማዕት ጋር በመሆን የፀረ ፋሺስት ትግሉን ተያያዙት። በተለይም የሠለጠነው የዑመር ሰመተር ጦር ገርለጉቤ ከተባለው ስፍራ ላይ መሽጎ ስለነበር እየተወረወረ ጠላትን መውጫ ቀዳዳ በማሳጣት ታላቅ ጀብዱ ፈፅሟል። ኤልቡር በተባለው ቦታ ላይ ዑመር ሰመተር በስድስት ባታሊዮን የጠላት ጦር ተከበቡ። የሠራዊታቸውን አቅምና የጦሩን ሁኔታ ተመልክተው ቦታ ለቀቁ፤ አንዳንድ ሰዎችም መሣሪያ አስረከቡ። ከአምስት ወራት በኋላ ዑመር ሰመተር ጦራቸውን አጠናክረው ሱማሌውን፣



ደጃዝማች ዑመር ሰመተር

> **« ... ቅኝ ገዢዎች በፈጠሩት ክፉ ሴራ አንዳንድ ሀገሮች እየተለያዩ ኖረዋል። የተለያዩትም በመጀመሪያ ከታሪክ ጋር ያልተያያዘ ድንበር በማበጀት፤ ቀጥለውም በሃይማኖትና በጎሳ እየተመካኘ ነው። ባሕል፣ ሃይማኖትና ቋንቋ አንዱን ወገን ከሌላው ሲለዩ የሚችሉ ምክንያቶች አይደሉም**

አማራውን፣ ትግሬውን፣ ኦሮሞውን እንዲሁም ከሌላው የአገሪቱ ግዛት የተውጣጣውን ኅብረተሰብ አስከትለው በ1930 ዓ.ም ገደማ አንድ ሌሊት በጠላት ጦር ላይ አደጋ ጣሉ። ስድስቱም ባታሊዮን የጣሊያን ጦር የሞተው ሞቶ ሌላውም ተማረከ። መሣሪያዎቹንም ማረኩና ተመልሰው ሺላቦ ላይ ሰፈሩ።

አሁንም የኢጣሊያ ጦር ሺላቦ ድረስ እየመጣ ቢያስቸግር እንደገና ገጥመው ድል አደረጉት። ብዙ የጠላት ጦር አባላትንም ገደሉ። ዑመር ሰመተር ከደጋው የኢትዮጵያ ክፍል በሚላክላቸው የሰው ኃይል፣ መሣሪያና ስንቅ እየተጠናከሩ እንደገና ቆራሄ ላይ ከጠላት ጦር ጋር ገጥመው አመድ አደረጉት። በመጨረሻም ከጠላት ምሽግ ውስጥ ገብተው የጨበጣ ውጊያ በማካሄድ ታላቅና የማይረሳ ገድል ፈፅመዋል።

ከዚህ በኋላ ወደ ደገሃቡር ተመልሰው ከበላይ አዛዦቻቸው ጋር ተገናኙ። በዚህም ወቅት የጦሩ የአንዱ ክፍል አዛዥ የነበሩት ደጃዝማች ገብረማርያም የዑመርን ጀግንነት ተመልክተው በኦጋዴን አውራጃ ካሉት የአካባቢው ተወላጆች ወታደር መልምለው እንዲቀጥሩ ፈቀዱላቸው። በዚህም ጊዜ የፊታውራሪነት ማዕረግ ተሰጣቸው። ፊታውራሪ ዑመር ሰመተር ጠላትን በማንበርከክ በገርለጉቤ፣ በቆራሄ፣ በሃነሌ ... የሚያስደንቅ ጀብዱ ፈፀሙ። ደጃዝማች አፈወርቅ ከሞቱም በኋላ ወታደሩን እያረጋጉ ሲዋጉ ቆይተው በመጨረሻ እርሳቸውም በስድስት ጥይት ቆስለው ስለነበር ወደ ጂግጂጋ ተመለሱ። ፊታውራሪ ዑመር ሰመተር የደረሰባቸው ቁስል እጅግ ከባድ ስለነበር ለጦርነት መሰለፍ ከማይችሉበት ደረጃ ላይ ደረሱ። የጦር መሣሪያ የሚገኝበትን ዘዴ እየቀየሱ፣ ሕዝቡም ካለው የማረሻ በሬና ሌላም ቁሳቁስ እያዋጣ በመሸጥ ጥይትና ጠመንጃ እየገዛ ትልቅ ውጤት አስገኝቶ ነበር።

በኋላም ቁስላቸው እጅግ እየበረታባቸው ስለሄደ ወደ ሐርጌሳ መሰደድ ግድ ሆነባቸው። ከሐርጌሳ ተነስተው ኬንያ ገቡ። ከኬንያ ወደ ለንደንም ተወስደው ነበር። ከዚያም የቀረውን የጦርነት ጊዜ በስደት ላይ ሆነው ካሳለፉ በኋላ ነፃነት ሲመለስ ወደ ሀገራቸው ገቡ። ስድስቱ ጥይት በአካላቸው ውስጥ እንዳለ ነበር ወደ ሀገራቸው የተመለሱት።

ነፃነት ከተመሰለ በኋላ አርበኛው ሁሉ እየፎከረና እያቅራራ ጀግንነቱን ሲያስመሰክር ፊታውራራ ዑመር ሰመተር በምድረ ኦጋዴን ከጦር የተረፉ ጀግኖች ናቸው ካሉበት በመብራት ያስፈለጓቸው። ቀጥሎም የደጃዝማችነት ማዕረግ ተሰጣቸውና የኦጋዴንና ጂግጂጋ ገዢ ሆኑ።

ይሁን እንጂ በአካላቸው ውስጥ ያሉት ጥይቶች እረፍት ነሳቸው፤ ቁስሉም እያመረቀዘ አስቸገራቸው። በሐረር ከተማ ሐኪሞች ባሉበት ቦታ ሁሉ እየተዘዋወሩ ቢታከሙም መዳን ግን አልቻሉም።

ደጃዝማች ዑመር ሰመተር ለአገራቸው ትልቅ ቁም ነገር ሠርተው መጋቢት 6 ቀን 1936 ዓ.ም፣ በተወለዱ በ65 ዓመታቸው አረፉ። ሥርዓተ ቀብራቸውም በሐረር ከተማ ውስጥ በወታደራዊ ክብር ተፈጽሟል።

ደጃዝማች ዑመር ሰመተር ከመሞታቸው በፊት እንዲህ ብለው ነበር። « ... የአገሬን ሕዝብ የፈጀው ጠላት በጀግኖች ክንድ ተረግጦ ሲወጣ በዓይኔ ተመልክቻለሁ። የመገዛት፣ የመዋረድና የመረገጥ እድል ምን እንደሆነ ዐይቻለሁ። እንደተራራ ንብ በየምሽጉ እየገቡ የሚነድፉ ኢትዮጵያውያን ዘር በመሆኔም ኮርቻለሁ። በታሪክ የሰማሁትን የዓድዋ ጀግኖች ጀብዱ ለማስመስከር ልጆቻቸው በኦጋዴን የጣሊያንን አንገት ሲቆርጡ አይቻለሁ። የዚህ ሕዝብ ልጅ በመሆኔ አሁንም እኮራለሁ። የማዝነው ግን መላው ሱማሌዎች ተባብረው የአንዲት ኢትዮጵያ ልጅ ሆነው በአንድ ሰንደቅ ዓላማ ስር ሲጠቃለሉ ሳላይ በመሞቴ ነው። በመቃብርም ውስጥ ምኞቴ ይህ ነው። »

ደጃዝማች ዑመር ሰመተር የባሕል፣ የሃይማኖትና የቋንቋ ልዩነት ለሀገር አንድነት መሰናክል መሆን እንደሌለባቸው ሲያስገነዝቡም « ... ቅኝ ገዢዎች በፈጠሩት ክፉ ሴራ አንዳንድ ሀገሮች እየተለያዩ ኖረዋል። የተለያዩትም በመጀመሪያ ከታሪክ ጋር ያልተያያዘ ድንበር በማበጀት፤ ቀጥለውም በሃይማኖትና በጎሳ እየተመካኘ ነው። ባሕል፣ ሃይማኖትና ቋንቋ አንዱን ወገን ከሌላው ሊለዩ የሚችሉ ምክንያቶች አይደሉም። በሕንድ በመቶ የሚቆጠሩ ሃይማኖቶችና ቋንቋዎች አሉ ሲባል ሰምቻለሁ፤ በሌሎቹም ሀገራት እንዲሁ። ይሁን እንጂ ሰዎች የተለያየ ቋንቋ በመናገራቸው ከመሠረታዊ ታሪክ ሊፋናቀሉ አይገባም። አሁንም ኢምፔሪያሊስቶች በምሥራቅ አፍሪካ ቀንድ የሚሸርቡት ሴራ ለታሪክ የተጋለጠ ነው። ጠላትን ተባብረን ከሀገራችን ያስወጣን ኢትዮጵያውያን ቅኝ ገዢዎች ቀብረውት የሄዱት ቦንብ ቀኑን ጠብቆ እየፈነዳ ወገን ከወገኑ ሊፋጅበት አይገባም። እኛ ሱማሌዎችም ከሌሎች ሱማሌዎች ጋር ተባብረን ከአንዲት ኢትዮጵያ ጋር ተቀላቅለን በሠላም መኖር አለብን።

ኦጋዴን በጦር ሜዳ፣ በሐረርም ጠቅላይ ግዛት በአስተዳዳሪነት ስላለሁ እንዳሁኑ የአልጋ ቁራኛ ሳልሆን ከሰሜን፣ ከምዕራብ፣ ከደቡብ እንዲሁም ከመሐል ኢትዮጵያ የመጡ የሀገሪቱን ተወላጆች ተመልክቻለሁ። ከነደጃዝማች ነሲቡ እና ከነደጃዝማች አፈወርቅ ጋር ሆኜ ተዋግቻለሁ። ሌላውን ኢትዮጵያዊ ከኦጋዴን ሱማሌ ወይም ከሌላው ሱማሌ የሚለየው አንዳችም ነገር አይቼ አላውቅም። ባሕል፣ ሃይማኖትና ቋንቋ ሌላ ጉዳይ ነው። ስለዚህ ምኞቴ በምሥራቅ ክፍላችን ያሉ የተበታተኑ ሱማሌዎች አንድ ሆነው ኢትዮጵያዊነታቸውን ሲያስከብሩ ይታየኛል። በጠመንጃ ሰደፍ ያስወጣነው ጠላት መልኩን ለውጦ ከእናት ሀገር ሊለይ ታሪክ ሠራሽ ሳይሆን ሰው ሠራሽ ችግር እየፈጠረ ነው። ሕዝባችን ይህን ተረድቶ አንድነቱን ማጠናከር አለበት ...» ብለው ተናግረው ነበር።

**እነሆ እኝህን ጀግና ታሪክ ሲዘክሩቸው ይኖራል።**

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

## ስቲያትር የታመነው ተፈራ ወርቁ

**ቤዛ እሸቱ**

በርካታ የሀገራችን ተዋናዮች ከፊልም ለቲያትር የተለየ ፍቅር አለን ይላሉ። ቲያትር ቀጥታ ከተመልካች ጋር ያገናኛልና ዛሬስ መድረክ ላይ ምን ይፈጠር ይሆን? በሚል ሁሌ ልብ ያንጠለጥላል። ደግሞም ከሳምንት ሳምንት ሳያወላዱ ለመድረክ ታምኖ መድረክ ላይ መገኘትን ይሻል። ይህ ሁሉ መስዋዕትነትን ቢያስከፍልም በሀገራችን ከቲያትር የሚገኘው ገቢ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ለዚህም ይመስላል በርካታ የሀገራችን የትወና ዘርፍ ሰዎች ቲያትር መጀመሪያቸው፤ ወደ ዝና መውጫቸው እንጂ የሚቆዩበት ሲሆን የማይታየው።

በሀገራችን የሚገኙ በርካታ የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች በሀገራችን "ስለቲያትር የለፋ አንድ ሰው ጥሩ" ቢባሉ በጋራ የሚጠሩት "ተፈራ ወርቁ" የሚል ይሆናል። ውልደቱና እድገቱ አዲስ አበባ፣ ቀጨኔ መድኃኒያለም ነው። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን አፍሪካ አንድነት፤ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በዳግማዊ ምኒሊክ ትምህርት ቤት ተከታትሏል።

የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሳለ በክበባት የነቃ ተሳትፎ ነበረው። የቲያትር "ሀ . . . ሁ"ን እንዲቆጥር በሕይወቱ ውስጥ ሁለት ተስፋዬዎች ትልቅ ቦታ ተጫውተዋል የመጀመሪያው የእውቀት መምህሩ ተስፋዬ ሲማ ነው። የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ ሳለ ከሚማርበትና አራት ኪሎ ከሚገኘው ዳግማዊ ምኒሊክ ትምህርት ቤት ወደ ሰፈሩ፣ ቀጨኔ መመላለስ የዘወትር ተግባሩ ነበር። በዚህ መሐል ተስፋዬ ሲማ ያስተምርበት የነበረው ቅድስት ማርያም አካባቢ የተለጠፈ "የቲያትር ፍላጎት ያላችሁ ለመሠልጠን ተመዝገቡ" የሚል ማስታወቂያ ያያል። ለመመዝገብ አላመነታም፤ ተመዝግቦም በርካታ የሥልጠናው ፈላጊዎች ነበሩና በፈተና ተጣርተው ካለፉ ጥቂቶች መሐል አንዱ በመሆን ወደ ስድስት ወር ለሚጠጋ ጊዜ የተሠጠውን ሥልጠና በብቃት ተከታትሏል። በቆይታውም መሠረታዊ የቲያትር ትወና፣ ዝግጅትና የአጻጻፍ ሥልትን ተምሯል። ሥልጠናውን ሲያጠናቅቅ የሎሬት ፀጋዬን "እናት ዓለም ጠኑ" ቲያትር ለታዳሚዎች ተውኖ ተመርቋል።

ከዚህ በመቀጠል የክብር ዶክተር ተስፋዬ አበበ (ፋዘር) ጋ በመሄድ ተጨማሪ እውቀት ቀስሟል። እዛ የመጀመሪያ የመድረክ ሥራው የሆነው "ሕይወት በየፈርጁ" ቲያትር ላይ በሀገር ፍቅር አዳራሽ የመተወን እድል ተፈጥሮለታል። ከዚህ በተጨማሪም በተለያዩ የክልል ከተሞች በመዘዋወር ቲያትር ላይ የመሳተፍ እድል ነበረው። ሁለቱ ተስፋዬዎች ለሥራው አስፈላጊው ሥነ-ምግባር እንዲኖረው፤ ሙያውን እንዲወደው አስተዋፅዖ ማድረጋቸውን ያነሳል። ከሁለቱ ተስፋዬዎች በተጨማሪ ከጋሽ አያልነህ ሙላት ጋርም ቀንዲል ቤተ-ተውኔት እያለ በተዋናይነት መሥራቱን ያስታውሳል።

ከተስፋዬ አበበ ክበብ ከወጡ በኋላ የቀሰሙትን እውቀት የሚተገብሩበት መድረክ እንዲሆናቸው በማሰብ ከጓደኛው ብርሀኑ ታዬ (ናፒ) ጋር በመሆን በሀገራችን የመጀመሪያ ቲያትር በሆነው "ፏቡላ" የቲያትር ክበብን አቋቁመው መንቀሳቀስ ጀመሩ። በዚህ ሂደትም በርካታ ታዳጊዎችን አቅፈው ወደ መንቀሳቀስ ተሸጋግረዋል። ተሳክቶላቸው በትልቅ መድረክ ቲያትርን ባያሳዩም በየቀበሌ አዳራሾች በመዘዋወር ድራማዎችን ተጫውተዋል። በወቅቱ የቲያትር ቡድኑ አባል ከነበሩት መካከል ተሻለ ወርቁ፣ ቴዎድሮስ ለገሰ፣ ደምሴ በየነ፣ ቅድስት ገብረሥላሴ ተጠቃሽ ናቸው። በሂደት ክበቡ ወደ "ገድሉ አሰግድ የቲያትር ክበብ" ተሸጋገረ።

ተፈራ ቲያትር ይወዳል፤ ነብስያው ወደ ተዋናይነቱ ብሎም ወደ አዘጋጅነቱ እየሄደ መሆኑ ተሰምቶታል። ቲያትርን መሥራት መፈለግ የሱ ብቻ ፍላጎት ሳይሆን አብረውት እውቀት የቀሰሙ፤ ብሎም በክበብ የሚንቀሳቀሱ ወጣቶች ፍላጎት መሆኑን ለመረዳት አልከበደውም። ቲያትርን ለመጫወት በሀገራችን የሚገኙት በጣት የማይሞሉ ቲያትር ቤቶች መቀጠር ለበርካቶች ብቸኛ አማራጭ ይመስል ነበር። ቲያትር ቤቶቹ ሁሉንም የመቅጠር አቅም እንደሌላቸው ሳይታለም የተፈታ ነው። እዚህ ጋ በግል ፕሮዲውስ የሚያደርጉ ግለሰቦችና ድርጅቶች ሚና ይጎላል። ችግሩ ማን መዋዕለ ንዋዩን አፍስሶ፤ ቲያትር ያዋጣኛል ብሎ ፕሮዲውስ ያድርግ። በዘርፉ በርካታ ተዋናይ፣ ደራሲ ብሎም አዘጋጅ አለ። በቂ ቀርቶ ጥቂት የሚባል ፕሮዲውሰርም ማግኘት ከባድ ነበር። ታዲያ ያኔ ያለውን ክፍተት ለመሙላት በማሰብ "ተስፋ የኪነጥበብ ኢንተርፕራይዝ"ን መሠረተ። ታዲያ ይህ መሆኑ ከትወናውና ከዝግጅቱ አርቆት ቆይቷል።



ለቲያትር ካለው ክብር የተነሳ የቲያትር ፌስቲቫል ለበርካታ ጊዜያት አዘጋጅቷል። ከዚህም ባሻገር "ተስፋ አዋርድ"ን በማዘጋጀት ትያትረኞችን በመሸለምም ይታወቃል።

በተፈራ የተቋቋመው ተስፋ የኪነጥበብ ኢንተርፕራይዝ በያዝነው ዓመት 25ኛ የምስረታ በዓሉን በተለያዩ ዝግጅቶች በማክበር ላይ ይገኛል። ኢንተርፕራይዙ በ25 ዓመታት ቆይታው 27 ቲያትሮችን ፕሮዲውስ በማድረግ ለተመልካች አቅርቧል። "የቲያትር ተመልካች ሸሸቷል"፤ "የሲኒማ እድገት ቲያትርን ውጦታል"፤ "የቴሌቪዥን ድራማዎች ቁጥር መጨመር የቀነሰውን የቲያትር ተመልካች ቁጥር ይበልጥ አሽቆለቆለው" በሚባልበት ወቅትም ተፈራና ቲያትር ላይለያዩ ቃል የተገባቡ ናቸውና በርካቶች ትግሉ መሯቸው ከመድረኩ ቢርቁም እሱ ግን ለቲያትር እንደታመነ ቆይቷል። በዚህም በሙያ ወዳጆቹ ዘንድ "ተፈራ ለቲያትር የታመነ" የሚል ሥያሜን አስቸሮታል።

ባለፉት 25 ዓመታት ኢንተርፕራይዙ 27 ትያትሮችን ፕሮዲዩስ አድርጎ ለእይታ ያቀረበ ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቲያትር በበጀት እጥረት ምክንያት ያቋረጠው "የቴዎድሮስ ራዕይ" ቲያትር ይገኝበታል። ቲያትሩ መጀመሪያ በአማራ ክልል ፕሮዲውሰርነት በባሕርዳር፣ ሙሉለም አዳራሽ ሲታይ ቆይቶ በድጋሚ በብሔራዊ ቲያትር አማካኝነት ከአንድ ዓመት በላይ ማሳየት ተችሏል። ትያትሩ ከ150 በላይ ተዋናዮች የሚሳተፉበትና ስለኢትዮጵያ አንድነት የሚያወሳና በብዙኃኑ የሚወደድ ነው። ሆኖም ብሔራዊ ቲያትር በወጪው መብዛት ምክንያት ከአንድ ዓመት በላይ ማሳየት አልቻሉም። ይሄ ቲያትር ተቋርጦ እንዳይቀር በሚል ተስፋ ኢንተርፕራይዝ የቲያትሩን አዘጋጅና ደራሲ ጌትነት እንየው በማናገር በኢንተርፕራይዞች ባልተለመደ መልኩ ማሳየት ችለዋል።

ቲያትሩ መድረክ ላይ በነበረበት ወቅት ከቲያትሩ የመግቢያ ዋጋ በተጨማሪ የተወሰኑ ድርጅቶች ስፖንሰር በመሆን አግዘዋል። በዚህም ለ150ውም ተዋናዮች፣ ለደራሲውና ለአዘጋጁ፤ እንዲሁም፣ ለቲያትር ቤቱ ክፍያ በመፈጸም ምንም እንኳን ኢንተርፕራይዙ ትርፍ ባያገኝም፣ በኢንተርፕራይዝ ደረጃ በርካታ ተዋናይ የሚሳተፍበት ቲያትር ማሳየት እንደሚቻል ለማሳየት መሞከራቸውን ይናገራል። በሀገራችን ኢንተርፕራይዞች ዘንድ ቁጥብ ገጸ-ባሕሪ ያላቸው ቲያትሮችን መምረጥ እንደ ዓላማ የተያዘ መሆኑን በመጥቀስ የእሱ ኢንተርፕራይዝ ግን በትንሹ ስድስት ሰው ከማሳተፍ አንስቶ እስከ 150 ሰው የሚተውንበት ቲያትር እንደሚያሳዩና የቲያትር ተመልካቹ ጥሩ ቲያትር በማየት መደሰት አለበት የሚል አቋም እንጂ ከትርፍ አንጻር ብዙ እንደማይጨነቁ ያነሳል።

የቴዎድሮስ ራዕይ፣ የሌሊት ሙሽሮች፣ ሠማያዊ ዓይን፣ የብዕር ሥም፣ ጥቁር ፈተና፣ የተዋቡ እጆች፣ ፍርሀት፣ ምስጢረኞቹ፣ ያመረቀዘ ልብ፣ የጠለቀች ጀንበር፣ ሩብ ጉዳይ በተስፋ ኢንተርፕራይዝ አማካኝነት ለዕይታ ከበቁ ትያትሮች ጥቂቶቹ ናቸው። ተስፋ የኪነጥበብ ኢንተርፕራይዝ በተለይ በ90ዎቹ ከቲያትርም ባሻገር ትልልቅ የሙዚቃ ኮንሰርቶችን በማዘጋጀት ትልቅ ሥም ገንብቷል። ኢንተርፕራይዙ ባዘጋጀው ኮንሰርት ላይ ከሙዚቃው ንጉሥ ጥላሁን ገሠሠ አንስቶ እስከ ትንሹ ጥላሁን በመባል እስከሚታወቀው አብነት ግርማ ድረስ ያልሠራ ድምፃዊ የለም። በጥቂቱ ለማስታወስ ያህል፤ ጎሣዬ ተስፋዬ፣ ዓለማየሁ ሂርጶ፣ ቴዲ አፍሮ፣ ላፎንቴኖች፣ ፀጋዬ እሸቱ፣ ተፈራ ነጋሽ፣ ፍቅርአዲስ ነቅዓጥበብ፣ ምኒሊክ ወስናቸው፣ ታምራት ሞላ አብረዋቸው ከሠሩ በርካታ ድምፃውያን መካከል ጥቂቶቹ ናቸው። ኢንተርፕራይዙ በ1990ዎቹ አንድ ድምፃዊ ካሴት አወጣ ሲባል ኮንሰርት በማሠራት ይታወቃል። ያኔ በዋናነት ኮንሰርቶች ይዘጋጁ የነበሩት በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል ነበር። በመሐል በዋጋ መጨመርና ኢንተርፕይራዙ ወደ ቲያትር ይበልጥ በማድላቱ ከሙዚቃ ኮንሰርት ጋር ተለያይተው ቆይተዋል። ተፈራ አሁን ግን እንደ ድሯቸው የሙዚቃ ኮንሰርቶችን ለማዘጋጀት መዘጋጀታቸውንና ለዚህም ከዚህ ቀደም ያካበቱት ልምድ እንደሚያግዛቸው ያነሳል።

ተስፋ ኢንተርፕራይዝ ላለፉት 25 ዓመታት በኪነ-ጥበብ ዘርፍ፤ በተለይ በቲያትርና ሙዚቃ ሰፊ እንቅስቃሴ ሲያደርግ ቆይቷል። በተለያየ ጊዜ የተመሠረተበትን ዓመት ማክበር ቢፈልጉም በተለያዩ ምክንያቶች ይህን ማድረግ ሳይችሉ ቆይተዋል። ዘንድሮ ግን የ25ኛ ዓመት ክብረ-በዓላቸውን ከመስከረም ጀምሮ ማክበር ጀምረዋል። ከበጎ ዓላማዎች ጀርባ የማይጠፋው ተፈራ የድርጅቱን 25ኛ ዓመት ክብረ በዓል በበጎ ሥራ ማክበር ጀምሯል።

ከታኅሣሥ 22 እስከ ታኅሣሥ 28 ቀን 2016 ዓ.ም "በሊፍት ከፍዬ እሳፈራለሁ፤ በጎዳና የሚኖሩ ወገኖቼን አነሳለሁ" በሚል መሪ ቃል በአዲስ አበባ በተመረጡ ሞሎችና ትላልቅ ፎቆች የሕንጻውን ባለቤቶች በማስፈቀድ ተገልጋዮች አነስተኛ ክፍያ እየከፈሉ እንዲሳፈሩ በማድረግና በዛውም ከታዋቂ አርቲስቶች ጋር የሚተዋወቁበት መድረክ በመፍጠር የተገኘውን ገቢ ለሜሪጆይ እንዲሆን የራሳቸውን አስተዋፅዖ ማበርከት ችለዋል።

የድርጅቱን 25ኛ ዓመት ክብረ በዓል ዓመቱን ሙሉ የመቀጠል እቅድ ሲኖራቸው በዚህም ቲያትር የማሳየት፣ የበጎ አድራጎት ሥራዎችን የመሥራትና የተለያየ ዝግጅቶችን የማዘጋጀት እቅድ ይዘዋል። የመጨረሻው በዓል ግንቦት 26 በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቲያትር ሲሆን፤ ከዛ ቀድሞ ሚያዝያ 28 የቲያትር ፕሮግራም ይኖራቸዋል።

ድርጅቱ ቲያትር ላይ እንደመቆየቱ የተመረጡ ቲያትሮችን የማሳየትና ክብረ በዓሉ ቲያትርን ማዕከል ያደረገ እንዲሆን ታቅዷል። በ25ኛ ዓመት የበዓል መዝጊያ ፕሮግራም ላይ አንጋፋ ባለሙያዎች የሚከበሩበትና የሚሸለሙበት ከድርጅቱ ጋር አብረው የሠሩ ድርጅቶች የሚሸለሙበት የምስጋና ፕሮግራም በመሆን ግንቦር 26 ቀን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቲያትር በሙዚቃና በቲያትር በታጀበ መልኩ ተጋባዥ ሰዎች ባሉበት ለማክበር ማሰባቸውን ይገልጻል።

የጥበብ ዓለምን ሲቀላቀል ጅማሬው በትወና ቢሆንም አሁን ግን ዋነኛ የተፈራ መታወቂያው ፕሮዲውሰርነቱና የቲያትር አዘጋጅነቱ ሆኗል። በርካታ ትያትሮች ላይ በትወና ሲሳተፍ የቆየ ቢሆንም በቴሌቪዥን መስኮት ግን "ዳና" ድራማ ላይ ብቻ መተወኑን ይናገራል። ቢሆንም ድራማው ረዥም ጊዜ በመቆየቱና የተለየ ገጸ-ባሕሪን ይዞ በመተወኑ ከአንዳንድ ተመልካቾች ጠፋህ የሚል አስተያየት ይደርሰዋል። ሆኖም በርካታ ድራማዎችን ባለመሥራቱ ለብዙኃኑ እንግዳ መሆኑን፤ የሱ እውቅና በብዛት በዘርፉ ያሉ ሰዎች ጋር እንደ ሆነ ይናገራል። በርካታ ቲያትሮች ላይ ተውኗል፤ ቲያትር አዘጋጅቷል፤ ጽፏል። ከዚህም ባሻገር የሙዚቃ ኮንሰርቶችን በማዘጋጀት ይታወቃል። ያም ቢሆን ከትወና ዓለም መራቁን በማስመልከት "በብዙኃኑ ዘንድ ጠፋህ የምባል ተዋናይ አይደለሁም፤ ምክንያቱም ቲያትሮች ላይ እንጂ በፊልምና በቴሌቪዥን ትወና ብዙ አልሠራሁምና" ይላል። ሆኖም የቲያትር መድረኮች ላይ በተዋናይነት የመመለስ እቅድ አለው።

ለበርካቶች ቲያትር መነሻቸው እንጂ መድረሻቸው አይደለም። ለተፈራ ግን ቲያትር መነሻው ብቻ ሳትሆን መድረሻውም ነች። "በርካቶች ከገቢውም ጋር ተያይዞ መዳረሻቸው ፊልም ሲሆን እያየን ነውና አንተስ ምን አስበሀል?" አልነው። እሱ ግን አሁንም ሀሳቡ ከቲያትር አልወጣም። "እኔ ቲያትር በጣም እወዳለሁ፤ ለዚህም ቲያትርን እንድወድ ያደረጉኝ መምህራንም አሉ። ከዚህም በተጨማሪ ከልጅነቴም አንስቶ በብዛት የሠራሁት ቲያትርን ነው። " ይላል። ስለዚህም ሀሳቡ ቢሳካላት ቲያትርን ፕሮዲውስ ከማድረግም በዘለለ የግል ቲያትር ቤት እስከማቋቋም ያልማል። ኢንተርፕራይዙ 25 ዓመት የቆየ ቢሆንም ምን አለው? ሲባል መልሱ ምንም ነው። ሥም ከመትከል ውጭ ከኢኮኖሚ አንጻር የተጠቀመው ነገር አለመኖሩን ያነሳል። ያም ቢሆን ያለማቋረጥ መሥራታቸውንና ሌላው ቀርቶ በኮቪድ ጊዜ ተመልካች ባልነበረበትም ወቅት ቲያትርን መሥራት ቀጥለዋል። በርካታ ተዋንያንና ሌሎች ባለሙያዎችም በኢንተርፕራይዙ አማካኝነት የመሥራት እድል ማግኘታቸውና መታወቃቸው እርካታ ይሰጠኛል ይላል።

በአሁኑ ወቅት በብሔራዊ ቲያትር የሎሬት ፀጋዬ ድርሰት የሆነው "ሀሁ ወይም ፐፑ" ቲያትር በቀድሞ መምህሩ ተስፋዬ ሲማ ተዘጋጅቶ በተስፋ ድርጅት ፕሮዲውስ ተደርጎ ብሔራዊ ቲያትር በመታየት ላይ ይገኛል። ድርጅቱ ከተመሠረተበት ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ ያለማቋረጥ ቲያትር እያሳየ ዘልቋል። ለዚህም ሙያውን መውደድና ማፍቀር ካልሆነ በስተቀር የተለየ የኢኮኖሚ ጥያቄም፤ ጥቅምም አልነበረውም። ቲያትርን ትቶ ወደ ሌላ ዘርፍ መሄድ የማይታሰብ ሆኖበታል። አንድ ጊዜ ፊልም መሥራታቸውን በማስታወስ ፊልም ለኛ የሚሆን አይደለም" በማለት መተዋቸውን ይናገራል።

25 ዓመት ሙሉ ከቲያትር ጋር ቢቆራኙም በርካታ ተግዳሮቶች መኖራቸውን ያነሳል። የተዋናይ ልምምድ ተጠናቆ መድረክ የሚጠብቅ ቲያትር በግምገማ መውደቅ፤ የተዋናይ መቅረት ከፈተናዎቹ መሐል ይገኙበታል። ከዚህ ቀደም "ወርቃማ ፍሬ" የተሰኘ ቲያትር ዝግጅቱ ተጠናቆ በአዲስ አበባ ቲያትርና ባሕል አዳራሽ ለገምጋሚዎች ሲቀርብ "ቲያትር ቤታችንን አይመጥንም" በሚል እንዳይታይ መወሰኑን ይናገራል። በዚህ ሰዓት ለቲያትሩ የተመለመሉ ተዋናዮች ረዥም ጊዜ ሰጥተው ተለማምደዋል፤ ለቲያትሩ የሚያስፈልጉ በርካታ ግብዓቶች ግዢ ተፈጽሟል። ሆኖም ከምንም በላይ ያሳሰበው የተዋናዮቹ ሞራል ነበር፤ የለፉት ተዋናዮች ለፍተው ሜዳ ከሚቀሩ በሚል በወቅቱ ይሠራበት በነበረው ሜጋ ቲያትር ለተወሰነ ጊዜ እንዲታይ አድርጓል። ረዥም ጊዜውን ለቲያትሩ ሰጥቶ የተለማመደ ተዋናይ ቲያትሩ ወደ መድረክ ሊወጣ ሲል መታመም ከሳንካዎቹ መሐል ይገኝበታል። በመንግሥት ቲያትር ቤቶች ያለው ዝቅተኛ የመግቢያ ዋጋ በዘርፉ ለመቆየት አበረታች አለመሆኑን ይናገራል።

ያኔ ተፈራ ኮንሰርት በሚያዘጋጅበት ወቅት ከአንጋፋ ድምፃዊያን አንስቶ ገና ብቅ ያሉ ድምፃውያንን ከማሳተፉም ባሻገር በኮንሰርቶቹ ላይ የአስቂኝ አለባበስ ትርዒት፣ የጥርስ ወላቃዎች ውድድር፣ የዳንስ ውድድር በተጓዳኝ በማዘጋጀት ኮንሰርቱን ወደ አዝናኝ ሁነት የመቀየር ልምድ ነበራቸው። በተጨማሪም በድምፁ እንጂ በመልክ የማይታወቅ የነበረውን አለምነህ ዋሴ መድረክ መሪ እንደሚሆን በማስተዋወቅ፤ እንዲሁም በ"የማዕበል ዋናተኞች" የሬዲዮ ድራማ ዝነኛ የነበሩት በገጸ-ባሕሪ ሥማቸው እፁብና ጌትን እንግዳ እንደሚሆኑና የተለያዩ የማስታወቂያ መንገዶችን ስለሚጠቀም የሱ ኮንሰርት ሁሌ ሙሉ ነበር። በቀጣይ ወደ ጠፋበት ኮንሰርት በመመለስ ኮንሰርቱን እያዘጋጁ በሚያገኙት ገቢ ቲያትሩን የመደጎም እቅድ አላቸው።

ተፈራ ለቲያትር ካለው ፍቅር እኩል የሚነሳው በኪነ-ጥበብ ዓለም ያሉ ሰዎች ሲቸገሩ ቀድሞ በመድረስ ነው። ለዚህም በቅርቡ በሞት ያጣነው ዳይሬክተር አሸብር ሀብታሙ በሕመም ምክንያት ሥራ ፈቶ ችግር ላይ በወደቀበት ወቅት ቀድሞ ከደረሱት ሰዎች መሐል አንዱ ነው። ያኔ የቴዎድሮስ ራዕይ ቲያትርን የአንድ ቀን ገቢ ለሱ እንዲውል በማድረግ ለሙያ ባልደረባው አጋርነቱን በተግባር አሳይቷል። ለሙያ ባልደረቦቹ የሚደርሰው "በችግሬ ሰዓት ይደርሱልኛል ብዬ ሳይሆን ለሕሊናዬ ብዬ የማደርገው ነገር ነው። ሆኖም የዚህን ውጤት በቅርቡ እናቴ ያረፈች ጊዜ አይቸዋለሁ። " ይላል። የሱን ኃዘን ኃዘናችን ነው ብለው ከጎኑ የተገኙ ባልደረቦቹ በመብዛታቸው የተነሳ አስር ቀን ሙሉ ድንኳን ሳይፈርስ ኃዘን ለመቀመጥ ተገደዋል።

ለግለሰብ ችግር ከመድረስ ባሻገር ለሀገራዊ ዓላማም መድረስ የተፈራ መታወቂያው ነው። "ሩብ ጉዳይ" ቲያትር በተፈራ ወርቁ ድርጅት እይታ ላይ የሚገኝ ቲያትር ነበር። በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ተከስቶ በነበረው የእርስ በእርስ ጦርነት የተጎዱ ወገኖችን ለማሰብ "ሩብ ጉዳይ ለሀገር ጉዳይ" በሚል በትያትሩ ደራሲ ጋዜጠኛ ቴዎድሮስ ተክለአረጋይ የሚመራ የጋዜጠኞች ቡድን ሀሳቡን ይዞ የቲያትሩ አዘጋጅና ፕሮዲውሰር የሆነው ተፈራ ጋር ይመጣሉ። በሀሳቡ በመስማማት ሀሳቡን በጋራ አበልጽገው የቲያትሩ ተዋናዮች ጭምር ከፍለው ያዩት የመጀመሪያው ቲያትር በመሆን በርካታ ገቢ ማስገኘት ተችሏል። ተፈራም አዘጋጅና ፕሮዲውሰር ነኝ ሳይል ቲያትሩን ከፍሎ ታድሟል። ከቲያትሩ የተገኘውን ገቢ በአይነት እቃ በመግዛት ለተቸገሩ ወገኖች ቦታው ድረስ ማድረስ ችለዋል። በአሁኑ ወቅት ተፈራም ሆነ ኢንተርፕራይዙ የድርጅታቸውን 25ኛ ዓመት ማክበር ላይ ሙሉ ትኩረታቸውን ማድረጋቸውን በማንሳት በዓሉ እንደተጠናቀቀ በአዳዲስ ቲያትሮችና የሙዚቃ ዝግጅቶች ለመምጣት እየተዘጋጁ መሆኑን ይናገራል። እኛም እንኳን ለ25ኛ ዓመት የምስረታ በዓላችሁ አደረሳችሁ! በማለት አበቃን።

# ዓለም አቀፍ

## ቦይንግ በ787 ድሪምላይነር አውሮፕላኑ ላይ ያጋጠመ ክስተትን ተከትሎ ምርመራ ጀመረ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ላታም የተባለው አየር መንገድ ንብረት በሆነ ቦይንግ 787 ድሪምላይነር አውሮፕላን ላይ ያለ ቁልፍ በድንገት በመነካቱ በመንገደኞች ላይ ቀላል ጉዳት ካጋጠመ በኋላ ምርመራ ተጀመረ።

በዚህ ክስተት ምክንያትም የምርመራው ውጤት አስኪታወቅ ድረስ አውሮፕላን አምራቹ ቦይንግ የ787 ድሪምላይነር አውሮፕላን አብራሪዎች በአውሮፕላኑ ውስጥ ያለውን የመቀመጫቸውን ሁኔታ እንዲፈትሹ አሳስቧል።

ዘዎል ስትሪት ጆርናል እንደዘገበው የአውሮፕላኑ የበረራ አስተናጋጅ ባልታሰበ ሁኔታ የተጫነችው ቁልፍ የአብራሪውን መቀመጫ ወደ አውሮፕላኑ መቆጣጠሪያ አስፈንጥሮት፣ የአውሮፕላኑ አፍንጫም ቁልቁል ወደ መሬት እንዲያሽቆለቁል ምክንያት ሆኗል።

ከአውስትራሊያ ወደ ኒውዚላንድ በበረራ ላይ በነበረው በዚህ አውሮፕላን ላይ ባጋጠመው በዚህ ክስትት ምክንያት በርካታ መንገደኞች ከመቀመጫቸው ተፈናጥረው ከአውሮፕላኑ ጣራ ጋር መጋጨታቸው ተነግሯል።

ከቀናት በፊት የላታም አየር መንገድ ንብረት በሆነው በረራ ላይ ባጋጠመው በዚህ ድንገተኛ ሁኔታ ምክንያት 50 በሚደርሱ ተሳፋሪዎች ላይ ቀላል ጉዳት ደርሷል።

የክስተቱን ምክንያት ለማወቅም ምርመራ የተጀመረ ሲሆን፣ ቦይንግ የተመሳሳይ አውሮፕላኖች አብራሪዎች ከጉዞ በፊት የወንበራቸውን ሁኔታ እንዲፈትሹ መክሯል።

አንድ ተሳፋሪ ክስተቱን በተመለከተ ለቢቢሲ እንደተናገሩት በርካታ ሰዎች በጭንቅላታቸው ላይ የመጋጨት ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን እና በአውሮፕላኑ ኮርኒስ ላይም መሰበር ማጋጠሙን ገልጿል።




የአደጋ ጊዜ አገልግሎት ሠራተኞች ከክስተቱ በኋላ እንዳሳወቁት በተፈጠረው ድንገተኛ ሁኔታ ከተጎዱት መካከል አንድ ሰው በከባድ ሁኔታ ውስጥ ይገኛል ተብሏል።

ቦይንግ "በአውሮፕላኑ ላይ ስላጋጠመው ሁኔታ የሚገኘ ውጤትን ምርመራውን የሚያደርጉት ባለሥልጣናት የሚያሳውቁ ይሆናል" በማለት ዝርዝር ሁኔታ ከመግለጽ ተቆጥቧል።

ጨምሮም ለጥንቃቄ ሲባል የቦይንግ 787 ድሪምላይነር አውሮፕላኖች አብራሪዎች ከዚህ በፊት በወጣው የአብራሪዎች መቀመጫዎችን የመቆጣጠሪያ ቁልፎችን በተመለከተ በወጣው መመሪያ መሠረት ፍተሻ እንዲያደርጉ አሳስቧል።

ክስተቱ ያጋጠመው የቺሊ እና የብራዚል ንብረት የሆነው አየር መንገድ ላታም በበኩሉ "እየተካሄደ ያለውን ምርመራ ለመደገፍ ከባለሥልጣናት ጋር በትብብር እየሠራ" መሆኑን ገልጿል።

አውሮፕላኑ ከኒውዚላንዷ ኦክላንድ ከተማ ወደ ቺሊ ዋና ከተማ ሳንቲያጎ እንዲበር ፕሮግራም ተይዞለት የነበረ ሲሆን፣ ባጋጠመው ሁኔታ ምክንያት ጉዞው ተሰርዞ ወደ መጨው ማክሰኞ ተላልፏል።

ይህ ድንገተኛ ክስተት በቦይንግ አውሮፕላን ላይ ያጋጠመው ባለፈው ጥር ወር አንድ የቦይንግ አውሮፕላን በሩ ተገንጥሎ በተደረገ ምርመራ በሩ ከታሠረባቸው ብሎኖች መካከል የተወሰኑት አለመኖራቸው ከታወቀ በኋላ ነው።

በተጨማሪም ከጥቂት ዓመታት በፊት በቦይንግ የምርት ደኅንነት ደረጃ ላይ ጥያቄዎችን በማንሳት የድርጅቱን ምሥጢር ያጋለጠው የቦይንግ ሠራተኛ በዚህ ሳምንት አሜሪካ ውስጥ ሞቶ መገኘቱ ይታወቃል።

ከጥቂት ሳምንታት በፊት ቦይንግ 737 ማክስ 9 አውሮፕላን በረራ ላይ ሳለ የአደጋ ጊዜ መውጫ በሩ የተገነጠለው አራት ብሎኖች ጎድለውት ነው መባሉ የሚታወስ ነው።

የአሜሪካ ብሔራዊ የትራንስፖርት ደኅንነት ቦርድ ክስተቱ ያጋጠመው አውሮፕላን ዙሪያ ያደረገውን የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት ባወጣበት ወቅት ነው።

ሪፖርቱ የአደጋ ጊዜ መውጫ በሩን አስረው መያዝ የነበረባቸው አራት ብሎኖች በቦታቸው አልነበሩም ካለ በኋላ ለመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርቱ ምላሹን የሰጠው አውሮፕላን አምራቹ ቦይንግ ለችግሩ ተጠያቂው እኔ ነኝ ማለቱ በወቅቱ ተዘግቧል።

የቦይንግ ፕሬዚዳንት ዴቭ ካልሁን "ከፋብሪካችን በሚወጣ አውሮፕላን ላይ ይህ አይነት ነገር መከሰት የለበትም። ለደንበኞቻችን እና ለተሳፋሪዎቻቸው የተሻለ ነገር መሥራት አለብን" ካሉ በኋላ አየር መንገዶች በቦይንግ ላይ እምነት እንዲኖራቸው አጠቃላይ እቅድ አውጥተን እየተገበርን ነው ብለው ነበር።

ንብረትነቱ የአላስካ አየር መንገድ የሆነው 737 ማክስ 9 አውሮፕላን ለበረራ ከተነሳ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ የአደጋ ጊዜ መውጫ በሩ ከተገነጠለ በኋላ በአስቸኳይ ለማረፍ ተገዶ እንደነበር የሚታወስ ነው።

ቦይንግ ሠራሹ 737 ማክስ 9 አውሮፕላን ባለፉት ዓመታት መነጋገሪያ ሆኖ ቆይቷል። ከአምስት ዓመት በፊት በኢትዮጵያ እና ኢንዶኔዢያ ባጋጠመ አደጋ ምክንያት ከበረራ ታግዶ የነበረው ይህ ማክስ 737 ዝርያ መሆኑ ይታወቃል።




# ሕፃናትና ፓርላማቸው

መልካምሥራ አፈወርቅ

«ልጆችዬ!» እንደምን ከረማችሁ? ዛሬ በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ቆይታ እናደርጋለን። ለመሆኑ ፓርላማ ሲባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? የምታውቁ ካላችሁ መልካም። የማታወቁ ብትኖሩ ደግሞ ከዛሬው የልጆች ዓምድ ላይ ጥቂት ግንዛቤ እንደምታገኙ ተስፋ አለኝ፡፡

ልጆች «ፓርላማ» የሚለው ቃል የተገኘው ከፈረንሳይኛ ቋንቋ ነው። በተግባሩ ደግሞ የተወካዮች ምክር ቤት በሚባለው ክፍል የሀገሪቱ የሕግ አውጭ አካል በመሆን ይሠራል። ስለፓርላማ ምንነት ጥቂት ከነገርኳችሁ እናንተን ስለሚመለከተው የዛሬው ርዕስ ስለ ሕጻናት ፓርላማ ደግሞ ጥቂት ላውጋችሁ ፡፡

በሕገ መንግስቱ ድንጋጌ አንቀፅ 25 ላይ ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ስለመሆናቸው ተደንግጓል። በአንቀጽ 36 ላይ ደግሞ ሕጻናት በሕይወት የመኖርና የማደግ፣ ከማንኛውም የኃይል ጥቃትና ብዝበዛ፣ ከአድሎዓዊነት ነፃ የመሆን መብት እንዳላቸው ሰፍሯል። ከዚሁ ጋር ተያይዞም ሕጻናት በሚመለከታቸው ጉዳዮች ላይ ተሳትፎ የማድረግ መብቶቻቸው የተከበሩ ስለመሆኑ በግልጽ ተቀምጧል፡፡

ልጆችዬ! ለሕጻናት ከተሰጡ መብቶች መካከል ዛሬ የምንነጋገርበት የሕጻናት ፓርላማ አንዱና ዋንኛው ነው። በሀገራችን የሕጻናትን ተሳትፎ ለማረጋገጥ በርካታ እንቅስቃሴዎች ሲደረጉ ቆይተዋል። ይህን መሠረት በማድረግም በ1999 ዓ.ም በሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም አማካኝነት በደቡብ ክልል «ኮንሶ» ላይ የመጀመሪያው ሞዴል የሕጻናት ፓርላማ ሊመሠረት ችሏል ፡፡

የፓርላማው ዋንኛ ዓላማ የሕጻናትን መብትና ጥቅም ለማስከበር የሚያስችሉ አደረጃጀቶችን መፍጠር ነው። ይህ አደረጃጀት ደግሞ ወደፊት እናንተን መሰል ልጆች በሀገራቸው የልማትና ዴሞክራሲ እንቅስቃሴዎች ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ከፍተኛ እገዛ ይኖረዋል ፡፡

በኢትዮጵያ መጋቢት 18 ቀን 2014 ዓ.ም በሀገር አቀፍ ደረጃ በአዲስ መልክ የተቋቋመው የሕፃናት ፓርላማ ከሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች በተውጣጡ አባላት ተሳትፎ ተደርጎበታል። በተለያዩ ክልሎችም ፓርላማ የሕጻናት ፓርላማ ተቋቁሟል፡፡

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ፈርማ ያጸደቀቻቸው የሕጻናት



**በሀገራችን የሕጻናትን ተሳትፎ ለማረጋገጥ በርካታ እንቅስቃሴዎች ሲደረጉ ቆይተዋል፣**

መብቶች ኮንቬንሽን ተግባራዊ እንዲሆን የዚህ ፓርላማ አስተዋፅዖ ከፍ ያለ ነው። ፓርላማው በቀበሌ፣ በወረዳ በዞንና ክፍለ ከተሞች፣ በክልል ከተሞችና አስተዳደሮች፣ በትምህርት ቤቶች የተለያዩ የትምህርት ዘርፎች በየደረጃው መቋቋም ይችላል።

በሁሉም ክልሎች ደግሞ የራሱ አፈ ጉባኤ፣ ምክትል አፈ ጉባኤ፣ ጸሐፊና የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዎች አሉት። አባላቱ እንደማንኛውም የምክር ቤቱ ተመራጮች ከስማቸው አስቀድሞ «የተከበሩ» የሚል መጠሪያ ይኖራቸዋል።

ፓርላማው ለሥራ የሚጠቀምበት ደግሞ ምክር ቤቱ የሚገኝበትን ክልል ቋንቋ ይሆናል። እነዚህ አካላት ሕጻናትን አስመልክቶ በሚነሱ ማንኛውም ጉዳዮች ላይ የመነጋገርና የመወሰን መብት አላቸው፡፡

ልጆችዬ! በቅርቡ በኦሮሚያ ክልል አዳማ ከተማ በተካሄደ አንድ ጉባኤ ስለ ሕጻናት ፓርላማ የተነሱ አበይት ጉዳዮች ነበሩ ። በጉባኤው ላይ ከኦሮሚያ ክልልና፤ ከተለያዩ የፌዴራል መሥሪያ ቤቶች የተውጣጡ እንግዶች ተገኝተዋል። በዕለቱ የተከበሩ ተማሪ ቅዱስ ሞላ የፌዴራል ሕጻናት ፓርላማ አፈ ጉበኤ ለእንግዶቹ መልዕክታቸውን አድርሰዋል፡፡

ልጆች! የተከበሩ አፈ ጉባኤ ቅዱስ ሞላ ምን አሉ መሰላችሁ፡ - የዓለም ሕጻናት ኮንቬንሽን እንደ ኤሮፓውያኑ ዘመን አቆጣጠር በኅዳር ወር 1989 ላይ በተባበሩት መንግሥታት አፅዳቂነት በሥራ ላይ እንዲውል መደረጉን ተናግረዋል። ሀገራችን ኢትዮጵያም ይህን ስምምነት ፈርመው ከተቀበሉት ሀገራት መካከል አንዷ ስለመሆኗ ጠቁመዋል፡፡

አፈጉባኤው በትኩረት እንደገለጹት ሕጻናት በኮንቬንሽኑ የተሰጣቸውን መሠረታዊ መብቶችና መርሆች በሚገባ እንዲታወቁና እንዲተገበሩ ማድረግ ያስፈልጋል። እንዲህ መደረጉ ደግሞ የሕጻናትን ጥቅም በማስቀደም ማኅበራዊ ደህንነታቸውን ለማስከበር የሚያስችል ሥርዓትን ለመዘርጋት ያስችላል፡፡

በአሁኑ ግዜ በተለያዩ ችግሮች ውስጥ የሚገኙ በርካታ ሕጻናት መኖራቸውን አፈጉባኤው አስታውሰዋል። ለነዚህ ሕጻናት ትኩረት ለመስጠትም ኅብረተሰቡን ጨምሮ መንግሥትና የሚመለከታቸው ወገኖች በሙሉ ሊተባበሩ እንደሚገባም በአትኩሮት ተናግረዋል፡፡

ልጆችዬ! የኦሮሚያ ሕፃናት ፓርላማ ምክትል አፈ ጉባኤና የፌዴራል ፓርላማ አባል የተከበሩ ተማሪ ሮማን ካዋ በበኩላቸው «አለኝ» ያሉትን መልዕክት አድርሰዋል። እሳቸው እንዳሉት የሀገራችን ሕጻናት ጥራት ባለው ትምህርት በዓለም ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ከፍተኛ ጥረት በመደረግ ላይ ነው፡፡

እንደ አፈ ጉባኤዋ አባባል ሕጻናት የሀገር ተስፋ እንደመሆናቸው በሀገራችን የሕጻናትን መብት ለማረጋጋጥ የሚያስችሉ ሰፊ ሥራዎች ተከናውነዋል። ከነዚህ ተግባራት ዋንኛው ሕጻናት መብታቸውን የሚያስከብሩበት፣ ድምፃቸውን የሚያሰሙበት የሕጻናት ፓርላማ መመስረቱ ነው ፡፡

ልጆች! አፈጉባኤዋ የኦሮሚያ ክልል ተወካይ እንደ መሆናቸው ፓርላማው ከተመሠረተ ወዲህ በክልሉ የተከናወኑ ተግባራትን ጠቁመዋል። እሳቸው እንዳሉት የፓርላማው ኣባላት አቅመ ደካማ ለሆኑ እናቶች መኖሪያ ቤት በመገንባት በአረንጓዴው ልማት ችግኞችን ሲተክሉ ቆይተዋል። ከዚህ ባሻገር ሕጻናት በትምህርት ቤቶቻቸው የተለያዩ ክበባትን በማቋቋም ተሳትፏቸውን እንዲያሰፉ አድርገዋል። ለዚህም የፓርላማው አባላት ድጋፍና አስተዋፅዖ ከፍ ያለ ነው።

አፈጉባኤዋ አክለውም በአሁኑ ግዜ በሀገራችን የተለያዩ ቦታዎች በጦርነትና ረሀብ ምክንያት በችግር ላይ የሚገኙ ሕጻናት ስለመኖራቸው አስታውሰው ሁሉም ዜጋ ስለነዚህ ሕጻናት ትምህርትና በሕይወት ስለመኖር ግድ ሊለው ይገባል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ልጆችዬ በዚህ ጉባኤ የተለያየ ኃላፊነት ያላቸው የመንግሥት አካላት ተገኝተዋል። ከነዚህ መሐል ክብርት ዓለሚቱ ዑመድ በሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አንዷ ናቸው። እሳቸው ምን እንዳሉ ታውቃላችሁ? ሕጻናትንና ሴቶችን አስመልክቶ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

ሚኒስትር ዴኤታዋ በሕጻናት አያያዝና እንክብካቤ ዙሪያ ኅብረተሰቡ ትኩረት ሊያደርግ እንደሚገባ ጠቁመው፣ የተሟላ ሰብዕና ያለው አገር ወዳድ ዜጋን ለማፍራትም ሁሉም የድርሻውን መወጣት እንዳለበት አሳስበዋል። የዛሬ ሕጻናት የነገ ሀገር ተረካቢዎች፣ የወደፊት ተስፋዎች ናቸውና መብታቸው ሊከበር ማኅበራዊ ደህንነታቸውም ሊጠበቅ ይገባል ብለዋል፡፡

ልጆችዬ! ለዛሬ ስለሕጻናት ፓርላማና በዙሪያው ስለሚነሱ ቁምነገሮች ጥቂት ግንዛቤ እንዳገኛችሁ ዕምነቴ ነው። በሚቀጥለው ሳምንት በሌላ ርዕሰ ጉዳይ ቆይታ የምናደርግ ይሆናል፡፡ለሁላችሁም መልካም የእረፍት ቀን እንዲሆንላችሁ ተመኘሁ ሰላም !